# حكم السحر والكهانة

## የድግምት እና ጥንቆላን ብይን የተመለከተ አጭር መልዕክት

" በአማርኛ ቋንቋ የተተረጎመ | مترجم بلغة الأمهرية"

አዘጋጅ | تأليف

فضيلة الشيخ عبدالعزيز بن عبدالله بن باز

የተከበሩ ሸይኽ ዐብዱልዐዚዝ ቢን ዐብዲላህ ቢን ባዝ

ትርጉም | ترجمة

مركز رواد الترجمة

ሩዋድ የትርጉም ማዕከል

شركاء التنفيذ:

دار الإسلام　جمعية الربوة　رواد الترجمة　المحتوى الإسلامي

يتاح طباعة هذا الإصدار ونشره بأي وسيلة مع
الالتزام بالإشارة إلى المصدر وعدم التغيير في النص.

Telephone: +966114454900
ceo@rabwah.sa
P.O.BOX: 29465
RIYADH: 11557
www.islamhouse.com

بسم الله الرحمن الرحيم

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው

## መቅድም

ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ሰላትና ሰላም በአላህ መልእክተኛ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው እንዲሁም የእርሳቸውን ቅን ጎዳና በተከተለም ላይ ሁሉ ይስፈን። በመቀጠል፦

ድግምት ከከባባድ ወንጀሎች አንዱ ሲሆን አላህና መልእክተኛው የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንድንርቃቸው ካዘዙን ሰባት አደገኛ ኃጢአቶች መካከልም አንዱ ነው። ባለንበት ጊዜ ድግምት በተለያየ ቅርፅና አኳኃን ተንሰራፍቶ ይገኛል። አንዳንዴም በፊልሞች ውስጥ በመዝናኛ እና በኮሜዲ ስም ተወሽቆ፤ አንዳንዴ ደግሞ በዙህድ እና በከራማ ስም፤ አንዳንዴም በሸሪዓዊ ሩቃ ግርዶሽ ስር ተሰግስጎ፤ አንዳንዴ በህዝባዊ ህክምና እና በእፅዋት መተካከም በሚል እንዲሁም በመሳሰሉት ሁኔታዎች ቅርፁንና አኳኃኑን እየቀያየረ በይፋ ይወጣል። ይህ ደግሞ ሃይማኖታቸውን በተመለከተ እውቀት በሌላቸው ሰዎች ዘንድ የሚደበቅባቸው ጉዳይ ነው።

የሳዑዲ ዐረቢያ አስተዳደር ጠቅላይ ሙፍቲ እና የታላላቅ ዑለማዎችና የኢስላማዊ እውቀት ጥናትና ፈታዋ ምክር ቤት ዋና ሰብሳቢ የሆኑት ሸይኽ ዐብዱልዐዚዝ ቢን ዐብደላህ ቢን ባዝ አላህ ይዘንላቸውና - በኪታባቸው ካካተቱት የድግምትን ብያኔ ማብራራት እና ከእርሱም በማስጠንቀቅ እንዲሁም ጠንቋዮች ዘንድ መሄድ ያለው ኢስላማዊ ብይንን በተመለከተ የፃፉት ኪታባቸው በውስጡ ካለው ይዘት አንፃር የእስልምና ጉዳዮች፣ የወቅፍ፣ የዳዕዋ እና ኢርሻድ ሚኒስቴር የዚህ ኪታብ መታተምና መሰራጨትን መልካም መሆኑን ተረድቷል።

ይህ የድግምትንና የደጋሚዎችን እንዲሁም ወደጠንቋይ መሄድን ያለውን ብይን በተመለከተ የጻፉት የእኚህ ታላቅ ሸይኽ ኪታብ ሸይኹ ካላቸው በረካ የተለገሰው ከሆነው መልካም ጥረታቸው፣ ብዙዎችን ወደቀናው ጎዳና ዳዕዋ አድራጊዎች እንዲሆኑ፣ ዲናቸውንም እንዲገነዘቡ፣ ኢስላማዊ ህግጋትንም እንዲማማሩ፣ ከመጥፎ ነገርም ተጠንቅቀው ሊያስጠነቅቁ ዘንድ፣ በዲናቸው በኩል ንቁ እንዲሆኑ፣ ለሙስሊሞችም ቅን እንዲሆኑ፣ ታላቁን የአላህን ኪታብና የምርጡን ነብይ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ፈለግን አጥብቀው የሚይዙ እንዲሆኑ፣ የደጋግ ቀደምቶችን ፋና በሚገባ የሚከተሉ ሊሆኑና ያንንም ከሚቃረኑ ፋናዎች ሁሉ የራቁ እንዲሆኑ ከሚያደርጉት መልካም የማለማመድ ጥረት ቅንጫቢ ነው።

ይህቺ የተባረከች የሆነችው ሀገርም አስተዋይ መሪዎቿም የላቀው አላህ ያፅናቸው፣ የእርዳታ ሰበቡንና ተወፊቁንም እንዲሁም ማበርታቱንም ይግጠማቸው በዚህ መልኩ ነው የሚጓዙት። የተከበሩ እውቁ ሸይኻችን የኪታቡ ጽሐፊንም መልካም ምንዳውን አብዝቶ ይቸርልን።

አላህ ይህንን ኪታብ ያነበበ፣ ያዳመጠና የቃኘው ሁሉ በኪታቡ ተጠቃሚ ሊያደርገው ዘንድ፤ ሁላችንን ደግሞ የአላህን ኪታብና የነብዩን ሱና አጥብቀን የምንከተል እንዲያደርገን፤ የሸይጧንን ጉትጎታ ከመንግዶቹና ከተንኮሎቹም እንዲታደገን እንማፀነዋለን። እነሆ እርሱ ለዚህ ተማፅኖ የተገባ እውን ሊያደርገው ቻይም እርሱ ነውና። ወደ ቀናው መንገድ የሚመራውም እርሱ ነው። የአላህ ሰላትና ሰላም በነብያችን ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው እንዲሁም በመላው ተከታዮቻቸውም ላይ ሁሉ ይስፈን።

ዐብደላህ ቢን ዐብዱልሙሕሲን አት-ቱርኪ

የኢስላማዊ ጉዳዮች፣ ዳዕዋና ኢርሻድ ሚኒስቴር

## የድግምት እና ጥንቆላ ብይን እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮች[1]

ምስጋና ለብቸኛው አምላካችን አላህ የተገባ ነው። የአላህ ሰላትና ሰላምም ከእርሳቸው በኋላ ነብይ ለሌለው በነብያት መደምደሚያ ላይ ይስፈን። በመቀጠል፡-

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህክምና ሰበብ ጥንቆላንና ድግምትን ተግባራዊ የሚያደርጉ ሟርተኞች ቁጥራቸው ከመብዛቱና በአንዳንድ ሀገሮችም ከመሰራጨታቸው እንዲሁም ከማህበረሰቡ መካከል ጅህልናው የሚጠናበትን ተላላ መጠቀሚያ ከማድረጋቸው አንፃር ለአላህና ለባርያዎቹ በመቆርቆር ጉዳዩ ከአላህ ውጭ ባለ አካል መንጠልጠልና ለአላህና ለመልዕክተኛው የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንም መመርያ መጣስ በመሆኑ ለሙስሊሙም ይሁን ለኢስላም ያለውን አደገኝነት ግልፅ ማድረግን ወደድኩ።

ስለዚህም በአላህ በመታገዝ የሚከተለውን እላለሁ። መታከም የተፈቀደ ስለመሆኑ ሙሉ ስምምነት ያለበት ጉዳይ በመሆኑ ሙስሊሞች ለውስጥ ህመም፣ ለቀዶ ጥገና፣ ለነርቭም ይሁን ለመሳሰሉት ህመሞች ሁሉ ወደ ህክምና ሄዶ ሀኪሙም በህክምና ሳይንስ በሚያውቀው መሰረት በሽታውን መርምሮ ሐላል በሆኑ መድሃኒቶች በሚስማማው መሰረት መታከም ይቻላል። ምክንያቱም ይህ የተለመደውን ሰበብ ማድረስ በሚል ርዕስ ስር የሚታይ እንጂ በአላህ ላይ ያለ ተወኩል ጋር የሚቃረን አይደለምና ነው። ጥራት የተገባው የላቀው አላህ ደግሞ የሚያውቅ አውቆት ያላወቀ አላውቀውም እንጅ በሽታን እንዳወረደው ሁሉ መድኃኒቱንም አውርዷል። ጥራት ይገባውና የበሽታ መድሀኒቶችንም በሐራም (ክልክል በሆኑ ነገሮች) አላደረገም።

በመሆኑም የትኛውም ህመምተኛ ህመሙን እንዲያውቁለት በሚልም ቢሆን የሩቅ ምስጢር እናውቃለን ባይ ብለው ወደሚሞግቱ ጠንቋዮች ሊሄድ አይፈቀድለትም። ልክ የሚሞግቱትንም ነገር ማመን እንደማይፈቀድለት ሁሉ ማለት ነው። ምክንያቱም የጥንቆላ ንግግራቸውን የሚናገሩት ወይ በግምት አለበለዚያም ለፍላጎታቸው ጂኒዎች ሊያግዟቸው ዘንድ ጂኒዎችን

---

[1] የዚህ ጽሑፍ የተወሰነው ክፍል “መጅሙዕ ፈታዋ ወመቃላቱን ሙተነዊዓህ” በተሰኘው ኪታባቸው ክፍል ሶስት ላይ “የድግምት እና ጥንቆላ ብይን እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮች” በሚል ርእስ ተለቋል። ጽሑፍ በተሟላ መልኩ ደግሞ በአስተዳዳሪው በኩል “የድግምት እና ጥንቆላ ብይን የሚያትት መልዕክት” በሚል ርዕስ ታትሞ የወጣ ሲሆን በአል-የማኒያህ መጽሔት እና በኢስላማዊ ጥናት መጽሔት ላይም ተሰራጭቷል።

በማሳተፍ ነውና። እነዚህ የሩቅ ምስጢር እናውቃለን ብለው የሚሞግቱ እስከሆኑ ድረስ ክህደትና ጥመት ላይ ናቸው።

ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ማለታቸውን ሙስሊም ዘግበዋል፡- "ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ስለ አንዳች ነገር የጠየቀ ለአርባ ቀናት ሶላቱ ተቀባይነት የለውም።" አቡ ሁረይራ ረዲየላሁ ዐንሁ ባስተላለፉት ሐዲሥ ደግሞ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡- (ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ሟርተኛው የተናገረውን ያመነ ሰው ወደ ሙሐመድ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን- በተወረደው ክዷል።) አቡ ዳውድ ዘግበውታል፤ አራቱ የሱነን ባለቤቶችም እንዲሁ መልዕክቱን የዘገቡት ሲሆን አል-ሐኪም በተከታዩ ቃል ከነብዩ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን- ሶሒሕ ሆኖ መምጣቱን አረጋግጠዋል፡- (ሟርተኛ ወይም ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ጠንቋዩ የተናገረውን ያመነ ወደ ሙሐመድ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በተወረደው ክዷል።) ዒምራን ቢን ሑሰይን (ረዲየሏሁ ዓንሁ) የአላህ መልዕክተኛ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን - እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፈዋል፡- (ገድ የሚደረግለትም ይሁን ገድ የሚያስደርግ ወይም የሚጠነቁልም ይሁን የሚያስጠነቁል ወይም የሚደግምም ይሁን የሚያስደግም ሁሉ ከኛ አይደለም። ወደ ጠንቋይ ሄዶ ጠንቋዩ በተናገረው ያመነ በሙሐመድ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ላይ በተወረደው ክዷል።) አል-በዛር በጥሩ ሰነድ ዘግበውታል።

በእነዚህ የተከበሩ ሐዲሦች ወደ ጠንቋዮች፣ ሟርተኞች፣ ደጋሚዎችና መሰሎቻቸው ዘንድ ሄዶ እነርሱን መጠየቅም ይሁን በተናገሩት ማመን የተከለከለና ከባድ ዛቻ ያለበትም እንደሆነ እንረዳለን። በመሆኑም ባለስልጣናትና አቅምና ችሎታው ያላቸው የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ወደ ጠንቋዮች እና ሟርተኞች ዘንድ የሚሄዱ ሰዎችን ማውገዝና በእንዲህ አይነቱ ድርጊት ላይ በግብይትም ይሁን በሌላ መስክ የሚሳተፉ አካላትን ወደነርሱ የሚሄዱ ሰዎችንም የሚገባቸውን ያህል ከባድ ውግዘት ሊደርስባቸው ይገባል። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ላይ ትክክል ሆነው በመገኘታቸውም ይሁን ወደነርሱ በሚመጡ አላዋቂ ሰዎች ብዛት መታለል አይገባም።

ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ወደ እነርሱ መሄድን፣ መጠየቅንና በተናገሩት ማመንን ከልክለዋልና ነው። የከለከሉትም ከሚያስከትለው ከባድ መዘዝ፣ አደገኛ ክፋት እና አስከፊ ፍፃሜ አንፃር እንዲሁም እነርሱም ክፉ ውሸታሞች በመሆናቸውም ነው። ልክ እንደዚሁ በእነዚህ ሐዲሦች ውስጥ ጠንቋይና ድግመተኛ ለመሆናቸው ማስረጃ አለ። ምክንያቱም ጠንቋይና ድግምተኛ የሩቅ ዕውቀት የሚሞግቱ በመሆናቸውና ግባቸው ላይ ሊደርሱ የሚችሉትም በጂኖች በመታገዝ በመሆኑ በጂኖች መታገዝ የሚችሉት ደግሞ እነርሱን በማስተናገድና ከአላህ ውጭ እነርሱን በማምለክ ስለሆነ ነው። ይህ ደግሞ ጥራት ይገባውና በአላህ ላይ መካድና በእርሱም ማጋራት ነው። የሚሞግቱትን የሩቅ

ዓዋቂነትን አምኖ የሚቀበል የነርሱ አምሳያ ነው። እነዚህን ጉዳዮች ከሚያከናውኑ ሰዎች ጋር የተሳተፈ ደግሞ የአላህ መልዕክተኛ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን - ከእንዲህ ዓይነቱ የጠሩ ናቸው። ማንኛውም ሙስሊም በመድሀኒት ሰበብ ለሚያነበንቡት መተትም ይሁን ለሚያስተምሩት ሌላ አጉል እምነት ነገር ተገዥ ሊሆን አይፈቀድለትም።

ምክንያቱም ይህ ሟርትና ሰዎችን ማታለል በመሆኑ ይህንንም ወዶ የተቀበለ ሰው በውሸታቸውና በክህደታቸው እርዳታውን እየለገሳቸው ነው። እንዲሁም ከሙስሊሞች መካከል የትኛውም ሰው ወደ እነርሱ ሄዶ ልጁን ወይም ሌላ ዘመዱን ለማን ማጋባት እንዳለበት ወይም በትዳር አጋሮች እና በቤተሰቦቻቸው መካከል ያለባቸውን የፍቅር፣ የመተማመንና የጥላቻ ሁኔታቸውን በተመለከተ ለመጠየቅም ቢሆን መሄድ በፍፁም የተከለከለ ነው።

ባለትዳሮቹ ያለባቸውን የመለያየትና የመሳሰሉት ሁኔታቸውን ለማወቅ ወደጠንቋዮቹ መሄዱ እንደማይፈቀደው ሁሉ ማለት ነው። ምክንያቱም ይህ ጥራት ከተገባው አላህ በቀር ማንም የማያውቀው የሩቅ ምስጢር ውስጥ የሚካተት ነውና።

ድግምት ልዕለ ኃያሉ አላህ ሁለቱን መላእክቶችን በተመለከተ በሱረቱል በቀራህ ላይ ከነገረንም እንደምንረዳው በክህደት ደረጃ እርም ከተደረጉ ሐራም ነገሮች መካከል ነው።

{وما يعلمان من أحد حتى يقولا إنما نحن فتنة فلا تكفر فيتعلمون منهما ما يفرقون به بين المرء وزوجه وما هم بضارين به من أحد إلا بإذن الله ويتعلمون ما يضرهم ولا ينفعهم ولقد علموا لمن اشتراه ما له في الآخرة من خلاق ولبئس ما شروا به أنفسهم لو كانوا يعلمون}[2].

"«እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም። ከእነሱም በሰውየውና በሚስቱ መካከል በርሱ የሚለዩበትን ነገር ይማራሉ። እነርሱም በአላህ ፈቃድ ካልሆነ በርሱ አንድንም ጎጂዎች አይደሉም። የሚጎዳቸውንና የማይጠቅማቸውንም ይማራሉ። የገዛውም ሰው ለርሱ በመጨረሻይቱ አገር ምንም እድል የሌለው መሆኑን በእርግጥ ዐወቁ። ነፍሶቻቸውንም በርሱ የሸጡበት ዋጋ ከፋ! የሚያውቁ በሆኑ ኖሮ (ባልሠሩት ነበር)።"[1]

እነዚህ የተከበሩ ጥቅሶች ድግምት ክህደት መሆኑን እና ደጋሚዎች በአንድ ወንድና በሚስቱ መካከል መለያየትንም የሚፈጥሩ መሆናቸውን ያመለክታሉ። ከዚያም ባሻገር ድግምት ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችለው በራሱ እንዳልሆነ ይልቁን ጥቅምም ሆነ ጉዳትን ሊያስከትል የሚችለው

---

[1] ሱረቱል በቀራህ አንቀጽ ቁጥር፡ 102

የአላህን ይሁንታዊ ፈቃድ እና ፍርድ ተከትሎ እንደሆነም ያመለክታል። ምክንያቱም ጥራት የተገባው የላቀው አላህ መልካሙንም እና ክፉውንም የፈጠረው እርሱ ነውና። ይህን እወቀቱ የወረሱት ከአጋሪዎች ነው፤ የማሰብ ችሎታቸው ደካማ በሆኑ ሰዎች ላይ የሚያለባብሱ ሰዎች ክፋታቸው እጅግ ከባድ ነው። ኢናሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂዑን። እነዚህ የተከበሩት አናቅፅ ድግምት የሚማሩ ሰዎች እየተማሩ ያሉት የማይጠቅማቸውን ብሎም የሚጎዳቸውን እንደሆነም ግልፅ አድርገዋል። አላህ ዘንድም ምንም አይነት ድርሻ እንደሌላቸው ማለትም፡ (እድለኝነት እና መልካም ምንዳ) የሌላቸው መሆኑን አስረድተዋል። ይህ ደግሞ በዱኒያም በአኺራም የሚገጥማቸው ክስረት አደገኛ መሆኑን የሚጠቁም ከባድ ዛቻ ነው። ራሳቸውንም በዝቅተኛ ዋጋ የሸጡ በመሆናቸው ልዕለ ኃያሉ አላህ እንዲህ ሲል ኮንኗቸዋል፦

{ولبئس ما شروا به أنفسهم لو كانوا يعلمون}

"ነፍሶቻቸውንም በርሱ የሸጡበት ዋጋ ከፋ! የሚያውቁ በሆኑ ኖሮ (ባልሠሩት ነበር)።"[1]እዚህ ጋ መግዛት የተባለው ራሳቸውን መሸጣቸው ለማለት ነው።

ከጠንቋዮች፣ ከሟርተኞችና እና ሌሎችም አጭበርባሪዎች ክፋት አላህ ይጠብቀን ዘንድ እንማፀነዋለን። ጥራት የተገባው አላህ ሙስሊሞችን ከክፋት እንዲጠብቃቸው፣ የሙስሊም መሪዎችንም እንዲጠነቀቋቸውና የአላህ ባርያዎች ከክፋታቸውም ከመጥፎ ስራዎቻቸውም ሰላም ሊሆኑ ዘንድ የአላህ ፍርድ ተግባራዊ ለማድረግ አላህ ይወፍቃቸው ዘንድ እንማፀነዋለን።

ጥራት የተገባው አምላካችን አላህ ድግምት ከመከሰቱ በፊት ከድግምቱ መጠንቀቅ የሚቻልበትን መንገዶች ለባሮቹ ደነግጎላቸዋል። ጥራት ይገባውና ለእነርሱ ካለው እዝነትና ከእነርሱ አንፃር ከተከሰተ በኋላ መታከም የሚቻልበትንም ግልፅ አድርጎላቸዋል።

ድግምት የሚያስከትለውን አደጋ ከመከሰቱ በፊት መጠንቀቅ የሚቻልባቸውንም ይሁን ከተከሰተ በኋላ መታከም የሚቻልባቸውን መንገዶች በሸሪዓም ከተፈቀዱት መካከል ተከታዮቹን መጥቀስ ይቻላል።

ድግምት ከመከሰቱ በፊት ከሚያስከትለው አደጋ መከላከል የሚቻልበትን መንገድ በተመለከተ፤ እጅግ አሳሳቢና አስፈላጊ ከሆኑት መካከል፦ በሸሪዓዊ ዚክሮች፣ በዱዓዎች እና ከነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በመጡ ከክፋት መጠበቂያ ውዳሴዎችን በመጠቀም

---

[1] ሱረቱል በቀራህ አንቀጽ ቁጥር 102

መከላከል፤ ከእነዚህም መካከል፡- ከግዴታ ሶላቶች በኋላ ልክ እንዳጠናቀቁ ከሚባሉት የተደነገጉ ውዳሴዎች በኋላ አየተል ኩርሲይን መቅራት፣ እንዲሁም በመኝታ ሰአት መቅራት ይቻላል። አየተል ኩርሲይ በቁርአን ውስጥ ካሉ አንቀፆች እጅግ የተከበረው አንቀፅ ሲሆን አያተል ኩርሲይ የሚባለው ተከታዩ አንቀፅ ነው፡-

{الله لا إله إلا هو الحي القيوم لا تأخذه سنة ولا نوم له ما في السموات وما في الأرض من ذا الذي يشفع عنده إلا بإذنه يعلم ما بين أيديهم وما خلفهم ولا يحيطون بشيء من علمه إلا بما شاء وسع كرسيه السموات والأرض ولا يئودهُ حفظهما وهو العلي العظيم}[4].

"አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ሕያው ራሱን ቻይ ነው። ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም። በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው። ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል። በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)። መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ። ጥበቃቸውም አያቅተውም። እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው።"[1]

ከእነዚህ መካከል፡- {قل هو الله أحد} {ቁል ሁወ አልሏሁ አሐድ}[2]፣ እና {قل أعوذ برب الفلق} {ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅን}[3] {قل أعوذ برب الناس} {ቁል አዑዙ ቢረቢንናስ}[4]የሚባሉትን እነኝህ ሶስቱን የቁርአን ሱራዎችን ከእያንዳንዱ ግዴታ ሶላት በኋላ መቅራት፤ ሶስት ሶስት ጊዜ ከፈጅር ሶላት፣ በሌሊቱ መጀመርያ ክፍል ማለትም ከመግሪብ ሶላት በኋላ፣ በመኝታ ሰአት መቅራት፤ እንዲሁም ተከታዩን የሱረቱል በቀራህ የመጨረሻዎቹን ሁለት አንቀፆችን በመጀመርያው የሌሊቱ ክፍል መቅራት፡-

{آمن الرسول بما أنزل إليه من ربه والمؤمنون كل آمن بالله وملائكته وكتبه ورسله لا نفرق بين أحد من رسله وقالوا سمعنا وأطعنا غفرانك ربنا وإليك المصير} [8]

{መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ። ምእምኖቹም (እንደዚሁ)። ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል

[1] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 255

[2] ሱረቱ አል-ኢኽላስ አንቀፅ ቁጥር፡ 1

[3] ሱረቱ አል-ፈለቅ አንቀፅ ቁጥር፡ 1

[4] ሱረቱ አን-ናስ አንቀፅ ቁጥር፡ 1

አንለይም» (የሚሉ ሲሆኑ) አመኑ። «ሰማን፤ ታዘዝንም። ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም።}[1] እስከ አንቀጹ መጨረሻ ድረስ።

የአላህ መልእክተኛ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን -እንዲህ ማለታቸውን በሶሒሕ ሐዲሥ ተዘግቧል፡- (በምሽቱ ክፍለጊዜ አየተል ኩርሲይን የቀራ ሰው እስኪነጋ ድረስ የአላህ ከለላ አይለየውም፤ ሸይጧንም አይቀርበውም።) እንዲህ ማለታቸውም በሶሒሕ ሐዲሥ ተላልፏል፡- (በሌሊቱ ክፍለ ጊዜ የሱረቱል በቀራን የመጨረሻ ሁለቱ አንቀፆችን ለቀራ ሰው በቂዎቹ ናቸው።) አላህ ይበልጡን ያውቃል ትርጉሙ፡- ከክፋት ነገር ሁሉ ይጠብቁታል ማለት ነው። ሌላው የአላህን ጥበቃ እናገኝባቸው ዘንድ በሸሪዓው የተደነገጉ (ፍፁም የሆኑ ከፍጡራኑ ክፋት የምንጠበቅባቸው) ውዳሴዎችን ሌትም ቀንም፣ በቤት ውስጥም ይሁን በበረሃ በህዋም ይሁን በባህር የአላህን ጥበቃ የሚያስገኙልን የተደነገጉ አዝካሮችን ማብዛት ነው።

ምክንያቱም ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ በማለታቸው ነው፡- የሆነ ቦታ ላይ ሲያርፍ "አዑዙ ቢከሊማቲላሂ-ት-ታማቲ ሚን ሸሪ ማ ኸለቅ" ያለ ሰው ከቦታው እስኪንቀሳቀስ ድረስ ምንም ነገር አይጎዳውም።) ትርጉሙ፡- ከፍጡራኑ ክፋት ፍፁም (ምሉእ) በሆነው በአላህ ቃል እጠበቃለሁ። እንዲሁም አንድ ሙስሊም በቀኑ መጀመሪያ እና በሌሊቱ መጀመሪያ ላይ ሶስት ጊዜ ተከታዩን ማለት፡- ("ቢስሚላሂ ለዚ ላየዱሩ መዓስሚሂ ሸይኡን ፊል አርዲ ወላ ፊሰማኢ ወሁወ ሰሚዑል ዓሊም" ትርጉሙ፡- ከስሙ ጋር በሰማይም በምድርም አንዳችም ነገር የማይጎዳበት በሆነው በአላህ ስም (እጠበቃለሁ)። እርሱም ሰሚ እና አዋቂው ነው።)

ይህንን የሚያበረታታ ሶሒሕ ሐዲሥ ከነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በመዘገቡ እና ይህም ከክፋት ሁሉ ለመጠበቅ ሰበብ በመሆኑም ነው። እነዚህ ውዳሴዎች እና መጠበቂያ ዚክሮች በቅንነት፣ በእምነት፣ በአላህ ላይ በመተማመንና በእርሱም ላይ በመደገፍ ለሚሰጡት መልዕክትም በአፅንኦት ልቡን ከፍቶ ለሚከታተላቸው የድግምትም የሌላውንም ክፋት ለመመከት ከታላላቅ ሰበቦች ከመሆናቸውም ባሻገር ድግምቱ ተደርጎ እንኳ ቢሆን እጅግ አብዝቶ ወደ አላህ ከመዋደቅና ጥራት የተገባው አምላካችን አላህን የተከሰተውን ክፋትና ችግር እንዲያስወግደው ከመማፀን ጋር ሆነው ድግምቱን ለማስወገድ ታላቅ ፈውስ ናቸው።

[1] ሱረቱ አል-በቀራህ፡ አንቀፅ ቁጥር፡ 285

የድግምትንም ይሁን ሌላን ህመም በማከም ረገድ ከነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ለመምጣታቸው ከተረጋገጡና ሱሐቦቻቸውንም ሲያክሙባቸው ከነበሩ ዱዓዎች መካከል፡- (“አሏሁምመ ረበ ናስ አዝሂቢል ባእስ ወሽፊ አንተ-ሽ-ሻፊ ላ ሺፋአ ኢላ ሺፋኡክ ሺፋአን ላዩጋዲሩ ሰቀማ” ትርጉሙም፡- የሰዎች ሁሉ ጌታ የሆንከው አላህ ሆይ! ችግሩን አንሳልን፤ ፈዋሹም አንተው ነህና ፈውስህን ለግስ፤ ካንተም ውጭ ፈዋሽ የለምና ምንም አይነት ስቃይን ያላስቀረ ፈውስህን ለግስ።) ይህንን ሶስት ጊዜ ማለት። ከእነዚህ ዱዓዎች መካከል ጂብሪል ዓለይሂ ሰላም ረሱል የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንን ሩቃ ያደረገበት ይገኝበታል፤ ይኸውም፡- (“በስሚላሂ አርቂከ ሚን ኩሊ ሸይኢን ዩእዚከ ወሚን ሸሪ ኩሊ ነፍሲን አው ዓይኒን ሐስድ፥ አሏሁ የሽፊከ ቢስሚላሂ አርቂከ” ትርጉሙ፡- በአላህ ስም አክምሀለሁ፤ ከሚያስቸግርህ አዛም ይሁን ከእያንዳንዷ ነፍስም ከምቀኛ ዓይን በአላህ ስም አክምሀለሁ፤ በአላህ ስም እፈውስሀለሁ አላህ ያሽርህ።) ይህንንም ሦስት ጊዜ ይደጋግመው።

ድግምቱ ከተከሰተ በኋላ ከሚደረጉ ሕክምናዎች መካከል ሌላኛው አንድ ሰው ከባለቤቱ ጋር ግንኙነት መፈፀም ከተቸገረ ሰባት የአረንጓዴ ቁርቁራ ቅጠል ወስዶ በድንጋይ ወይም በመሳሰሉት ፈጭቶ በአንዳች ነገር አድርጎ ለትጥበት የሚበቃውን ያህል በውሀ በመዘፍዘፍ በላዩ ላይ ተከታዮቹን የቁርአን አንቀፆችን ቀርቶ መተካከሙ ፋይዳው የጎላ ፈውስ ነው፡- አየተል ኩርሲይ፣ {ቁል ያአዩሃል ካፊሩን}[1]፣ {ቁል ሁወሏሁ አሐድ}[2]፣ {ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ}[3]፣ {ቁል አዑዙ ቢረቢናስ}[4]እንዲሁም በሱረቱል አዕራፍ የሚገኙ ድግምትን የተመለከቱ አንቀጾች ማለትም ተከታዮቹ አንቀፆች፡-

{وأوحينا إلى موسى أن ألق عصاك فإذا هي تلقف ما يأفكون. فوقع الحق وبطل ما كانوا يعملون. فغلبوا هنالك وانقلبوا صاغرين}

{ወደ ሙሳም፡- «በትርህን ጣል» ስንል ላክን። (ጣላትም) ወዲያውኑም የሚቀጣጥፉትን (ማታለያ) ትውጣለች። እውነቱም ተገለጸ። ይሠሩት የነበሩትም (ድግምት) ተበላሸ። እዚያ ዘንድ

[1] ሱረቱ አል-ካፊሩን አንቀፅ ቁጥር፡ 1

[2] ሱረቱ አል-ኢኽላስ አንቀፅ ቁጥር፡ 1

[3] ሱረቱ አል-ፈለቅ አንቀፅ ቁጥር፡ 1

[4] ሱረቱ አን-ናስ አንቀፅ ቁጥር፡ 1

ተሸነፉም፡፡ ወራዶችም ሆነው ተመለሱ፡፡}[1] በሱረቱ ዩኑስ ውስጥ ያሉ አንቀጾች ማለትም ተከታዮቹ አንቀጾች፡-

{وقال فرعون ائتوني بكل ساحر عليم. فلما جاء السحرة قال لهم موسى ألقوا ما أنتم ملقون. فلما ألقوا قال موسى ما جئتم به السحر إن الله سيبطله إن الله لا يصلح عمل المفسدين. ويحق الله الحق بكلماته ولو كره المجرمون}

{ፈርዖንም፡- «ዐዋቂ ድግምተኛን ሁሉ አምጡልኝ» አለ፡፡ ድግምተኞቹም በመጡ ጊዜ ሙሳ ለእነርሱ፡- «እናንተ የምትጥሉትን ነገር ጣሉ» አላቸው፡፡ (ገመዶቻቸውን) በጣሉም ጊዜ ሙሳ አለ፡- «ያ በርሱ የመጣችሁበት ነገር ድግምት ነው፡፡ አላህ በእርግጥ ያፈርሰዋል፡፡ አላህ የአጥፊዎችን ሥራ ፈጽሞ አያበጅምና፡፡» አላህም ከሐዲዎች ቢጠሉም እውነትን በቃላቱ ያረጋግጣል፡፡}[2] በሱረቱ ጣሃ ውስጥም ያሉት አንቀጾች፡-

{قالوا يا موسى إما أن تلقي وإما أن نكون أول من ألقى. قال بل ألقوا فإذا حبالهم وعصيهم يخيل إليه من سحرهم أنها تسعى. فأوجس في نفسه خيفة موسى. قلنا لا تخف إنك أنت الأعلى. وألق ما في يمينك تلقف ما صنعوا إنما صنعوا كيد ساحر ولا يفلح الساحر حيث أتى}

{«ሙሳ ሆይ! ወይ ትጥላለህ ወይም በመጀመሪያ የምንጥል እንሆናለን» (ምረጥ) አሉ፡፡ «አይደለም ጣሉ» አላቸው፡፡ ወዲያውም ገመዶቻቸውና ዘንጎቻቸው ከድግምታቸው የተነሳ እነርሱ የሚሮጡ (እባቦች) ኾነው ወደርሱ ተመለሱ፡፡ ሙሳም በነፍሱ ውስጥ ፍርሃትን አሳደረ፡፡ «አትፍራ አንተ የበላዩ አንተ ነህና» አልነው፡፡ «በቀኝ እጅህ ያለቸውንም በትር ጣል፡፡ ያንን የሠሩትን ትውጣለችና፡፡ ያ የሠሩት ሁሉ የድግምተኛ ተንኮል ነውና፡፡ ድግምተኛም በመጣበት ስፍራ ሁሉ አይቀናውም» (አልን)፡፡}[3]

በውሃው ላይ እንዲቀራበት የገለፅነውን ከቀራ በኋላ ሶስት ጊዜ ይጠጣበትና በቀረው ይታጠብ፡፡ በዚህም የአላህ ፈቃድ ታክሎበት በሽታው ይወገዳል፡፡ ሁለቴም ከዚያም በላይ መደጋገሙ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ በሽታው እስኪወገድ ድረስ ቢደጋገምም ችግር የለውም፡፡

[1] ሱረቱ አል-አዕራፍ አንቀፅ ቁጥር፡ 117-119

[2] ሱረቱ ዩኑስ አንቀፅ ቁጥር፡ 79-82

[3] ሱረቱ ጧሀ አንቀፅ ቁጥር፡ 65-69

እንዲሁም ድግምትን ከሚያክሙበት ዘዴዎች መካከል ሌላኛው - እጅግ ፋይዳቸው ከበዙት ፈውሶች ሲሆን - ድግምቱ የተቀበረበትን ቦታ በመሬት ላይም ይሁን በተራራ አልየም በሌላ ቦታ ለይቶ ለማወቅ መጣጣር ነው። ምክንያቱም ደግምቱ ያለበት ቦታ ከታወቀ አውጥተው ቢበታትኑት ድግምቱ ይከሽፋልና ነው።

ድግምትን መጠንቀቅና ማከም የሚቻልባቸው ዘዴዎችን በተመለከተ አላህ ያገራልን ይህን ይመስላል። አላህ ተውፊቁን ይግጠመን።

በድግምተኞች ስራ ማከሙ ማለትም በመስዋእት ወይም በሌላ አምልኮ ወደ አጋንንት መቃረቡ በፍፁም አይፈቀድም። ምክንያቱም ከሰይጣን ስራ ከዛም አልፎ ከባዱ ሽርክ ነውና። ይልቅ ተገቢው ነገር መጠንቀቁ ነው። ልክ ጠንቋዮችን፣ ሟርተኞችንና አጭበርባሪዎችንም እየጠየቁ መተካከሙና የሚሉትንም ተግባራዊ ማድረጉ እንደማይፈቀደው ሁሉ ማለት ነው። ምክንያቱም እምነተቢሶችና ቀጣፊ ሟርተኛ ጋጠወጦች በመሆናቸው ነው። የአላህ መልዕክተኛም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እነኝህ ሰዎች ዘንድ ከመሄድ፣ እነርሱን ከመጠየቅና የሚሉትን አምኖ ከመቀበል አስጠንቅቀዋል። ይህም ቀደም ብለን በዚህ ጽሑፍ መጀመሪያ ላይ እንደተገለጸው ነው። የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ድግምትን በድግምት ስለማክሸፍ ተጠይቀው እንዲህ ማለታቸው በሶሒሕ ሐዲሥ ተረጋግጧል፦ (“የሸይጧን ስራ ነው።” ኢማሙ አሕመድ እና አቡ ዳውድ በጥሩ ሰነድ ዘግበውታል። “ኑሽራ” ማለት ድግምትን በድግምት ማክሸፍ ማለት ሲሆን እሳቸው እንዲህ ሲሉ የፈለጉበት: “የጃሂሊያ ሰዎች ይጠቀሙበት የነበረውን የማክሸፊያ አይነት ማለትም ድግምትን ደጋሚ እንዲያከሽፈው አልያም ድግምቱን በአምሳያው ድግምት ማክሸፍን ማውገዛቸው ነው።

ሩቃ በማድረግ፣ በሸሪዓው የተደነገጉ በሆኑ ዱዓዎች እና በተፈቀዱ ፈውሶች ድግምትን ማክሸፉ ግን ቀደም ብለንም እንዳሳለፍነው ምንም ችግር የለውም። ይህም ታላቁ ሊቅ ኢብኑል ቀይም እና ሸይኽ ዐብዱረሕማን ኢብኑ ሐሰን ፈትሑል መጂድ በተሰኘው ኪታባቸው አላህ ይዘንላቸውና እንዲሁም ሌሎችም ሊቃውንት ያብራሩት ጉዳይ ነው።

አላህ ሙስሊሞችን በሙሉ ከመጥፎ ነገር ሁሉ እንዲታደጋቸው፣ ሃይማኖታቸውንም ለእነርሱ እንዲጠብቅላቸው፣ መገንዘቡንም እንዲለግሳቸው፣ የእርሳቸውን ድንጋጌ ከመጣስም እንዲያድናቸው አላህን እንማፀነዋለን። የአላህ ሰላትና ሰላም ባርያውና መልዕክተኛው በሆኑት ነብዩ ሙሐመድና በቤተሰቦቻቸውም ላይ ይስፈን።

## ሚስት ባሏ ላይ ያሰራቻው ድግምት[1]

ከዐብዱልዐዚዝ ቢን ዐብደላህ ቢን ባዝ ለተከበረው ወንድም... አሰላሙ ዓለይኩም ወራሕመቱሏሂ ወበረካቱህ በመቀጠል፡-

አላህ ቀናውን ጎዳና በመምራት ላይ ይድረስልዎትና በእለቱ የፃፉት ደብዳቤዎ እንዲሁም በውስጡ ያካተቱት አዲሷ ባለቤቶን ሊገናኙ ሲሉ ስላጋጠሞት ነገር፤ ወደ አንድ ሸማግሌ ሄደው የበፊቷ ባለቤቶ እርሶን ከግንኙነት ለማቀብ ስላደረገችው ነገር፤ ይህም ያለውን ፍርድ በተመለከተ መጠየቆንና የተሰጦትንም ምላሽ አስፍረውበት የላኩት ደብዳቤዎ ደርሶኛል።

ምላሹ: የቀድሞ ባለቤቶ ይህንን ድርጊት ለመፈፀሟ አምና ከተቀበለች ወይም በማስረጃ ከተረጋገጠ በርግጥ ከባድ ጥፋት ነው የፈፀመችው። ኧረ እንደውም! ጥመትም ክህደትም ነው የፈፀመችው። ምክንያቱም ይህ የእርሷ ድርጊት የተከለከለ ድግምት ነው። ድግምት የሚፈፅም ደግሞ ካፊር ነው። ልክ ጥራት የተገባው አምላካችን አላህ እንዲህ እንዳለን፡-

{واتبعوا ما تتلوا الشياطين على ملك سليمان وما كفر سليمان ولكن الشياطين كفروا يعلمون الناس السحر وما أنزل على الملكين ببابل هاروت وماروت وما يعلمان من أحد حتى يقولا إنما نحن فتنة فلا تكفر فيتعلمون منهما ما يفرقون به بين المرء وزوجه وما هم بضارين به من أحد إلا بإذن الله ويتعلمون ما يضرهم ولا ينفعهم ولقد علموا لمن اشتراه ما له في الآخرة من خلاق ولبئس ما شروا به أنفسهم لو كانو يعلمون}[ 17]،

{ሰይጣናትም በሱለይማን (ሰሎሞን) ዘመነ መንግስት የሚያነቡትን (ድግምት) ተከተሉ። ሱለይማንም አልካደም፤ (ድግምተኛ አልነበረም)፤ ግን ሰይጣናት ሰዎችን ድግምትን የሚያስተምሩ ሲኾኑ ካዱ። ያንንም በባቢል በሁለቱ መላእክት በሃሩትና ማሩት ላይ የተወረደውን ነገር (ያስተምሩዋቸዋል)። «እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም። ከእነሱም በሰውየውና በሚስቱ መካከል በርሱ የሚለዩበትን ነገር ይማራሉ። እነርሱም በአላህ ፈቃድ ካልኾነ በርሱ አንድንም ጎጂዎች አይደሉም። የሚጎዳቸውንና የማይጠቅማቸውንም ይማራሉ። የገዛውም ሰው ለርሱ በመጨረሻይቱ አገር ምንም እድል የሌለው መኾኑን በእርግጥ ዐወቁ። ነፍሶቻቸውንም በርሱ የሸጡበት ዋጋ ከፋ! የሚያውቁ በኾኑ ኖሮ (በልሠሩት ነበር)።}[2]ይህ የተከበረው አንቀጽ ድግምት ክህደት መሆኑን፤ ደጋሚም ከሀዲ

---

[1] ከታላቁ ሸይኽ ጽሕፈት ቤት በ9/11/1387 ዓ.ሂ መልስ የተሰጠበት

[2] ሱረቱ አል-በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 102

መሆኑን፤ ደጋሚዎች የሚማሩት የሚጐዳቸውን ብሎም የማይጠቅሟቸውን መሆኑን፤ ከእኩይ አላማዎቻቸው መካከል ባልየውን ከሚስቱ መለየት እንደሆነና በእለተ ትንሳኤም ምንም አይነት መልካም -የመዳኛ- ድርሻ የሌላቸው እንደሆኑ ያስገነዝባል። የአላህ መልዕክተኛ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንም - ሶሒሕ በሆነ ሐዲሥ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡- (ሰባት አጥፊ ወንጀሎችን ተጠንቀቁ።) "የአላህ መልእክተኛ ሆይ ምንድን ናቸው?" ሲባሉ እንዲህ በማለት መለሱ:- (በአላህ ማጋራት፥ ድግምት፥ አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ አግባብ ማጥፋት፥ ወለድ (አራጣ) መብላት፣ የየቲሞችን (አባታቸው የሞተባቸውን ልጆች) ገንዘብ መብላት፣ በተፋፋመ ፍልሚያ ወደ ኋላ መሸሽ፣ ጥብቅ (ንፁህ) (ከዝሙት ዝንጉ) የሆኑ ሴቶችን በዝሙት መቅጠፍ (መወንጀል) ናቸው።)

መድሀኒቱን የሰጠዎት ሽማግሌ ከሁኔታው መረዳት የሚቻለው እርሱም ሟርተኛ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም አስማተኞች ብቻ ካልሆኑ ማንም ተጨባጭ አሰራራቸውን የሚያውቅ የለምና ነው። ከዛም በላይ በብዙ ጉዳዮች ላይ የሩቅ ምስጢርን እናውቃለን ብለው ከሚሞግቱ አካላት መሆኑንም ጭምር መረዳት ይቻላል። ሙስሊም እነኝህን መሰል ሰዎች ሊጠነቀቃቸውና ስለ ሩቅ ምስጢር የሚሞግቱትንም አምኖ መቀበል የለበትም።

ምክንያቱም ነቢዩ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን- እንዲህ በማለታቸው ነው፡- (ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ስለ አንዳች ነገር የጠየቀ ሶላቱ ለአርባ ሌሊቶች ተቀባይነት የለውም።) ሙስሊም በሶሒሐቸው ዘግበውታል፤ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን- እንዲህም ብለዋል፡- (ሟርተኛ ወይም ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ጠንቋዩ የተናገረውን ያመነ ወደ ሙሐመድ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በተወረደው ክዷል።)

ማድረግ ያለብዎት ነገር ቢኖር የደረሰብዎትን ነገር በተመለከተ ተውባ እና መፀፀት ይገባል። ከዛም በተጨማሪ ሽማግሌውንና የቀድሞ ባለቤቶን በተመለከተ ፍርድ ቤት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድባቸው ወደ ፍርድ ቤትና አስተዳደር ማመልከት አለብዎ። ለወደፊቱ እንደዚህ አይነት ክስተት ሲያጋጥምህም ሸሪዓዊውን ፈውስ እንዲያመላክቱህ የሸሪዓ ሊቃውንትን ማማከር ይኖርብሀል። አላህ እኛንም እናንተንም የሃይማኖትን ግንዛቤ በዛውም ላይ ፅናቱንና እርሱን ከመቃረንም ሊታደገን ዘንድ እንማፀነዋለን። እርሱ ለጋስና ቸር ነውና።

ወሰላሙ ዓለይኩም ወራሕመቱሏሂ ወበረካቱህ (የአላህ ሰላምን አበረከት በአንተ ላይ ይሁን)

## ሟርተኞችንና አጭበርባሪዎችን መጠየቅ ያለው ኢስላማዊ ፍርድ[1]

ጥያቄ፡ ወንድም፡ ሰ. ዐ. በ. ከሪያድ ጥያቄው እንዲህ ይላል፡- በየመን አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ሰዎች “አለቆች” የሚሏቸው ከሀይማኖት ጋር የሚቃረኑ እንደ ጥንቆላ እና መሰል ነገራቶችን የሚፈፅሙ፣ መድሀኒት የላቸውም ለሚባሉ በሽታዎች መፈወስ እንደሚችሉም የሚሞግቱ እና ለዚህም እንደማሳመኛም ራሳቸውን በስለታማ ነገር እየወጉ አሊያም ጣታቸውን እየቆረጡ ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው ወደ ነበረበት መመለስ እንደሚችሉ የሚሞግቱ ሰዎች አሉ። ከመካከላቸውም የሚሰግዱም አሉ ከፊሎቹ ደግሞ አይሰግዱም።

እንዲሁም ከቡድናቸው ውጭ ላለ ሰው ማግባት ለራሳቸው የሚፈቅዱ ሲሆኑ ከነሱ ውጭ የሆነ ሰው ከነርሱ መካከል እንዲያገባ ግን አይፈቅዱም። ለህመምተኛ ዱዓእ ሲያደርጉም እንዲህ ነው የሚሉት፡- (አላህ ሆይ! እገሌ ሆይ!) ከአያቶቻቸው የአንዱን ስም ጠርተው ማለት ነው። ድሮ ድሮ ሰዎች ያከብሯቸዋል፤ እንደማንኛውም ሰው ሳይሆን እንደ ድንቅ ሰዎች ይቆጥሯቸውና ወደ አላህ ይበልጥ የቀረቡ አድርገው ያስቧቸውም ነበር። ከዛም አልፈው የአላህ ሰዎች ይሏቸውም ነበር። አሁን ላይ ግን ህዝቡ እነርሱን በተመለከተ ያለው አቋም ተለያይቷል፤ አንዳንዶቹ ይሀውም የወጣቱ ክፍል እና አንዳንድ የዒልም ሰዎች ይቃወሟቸዋል፤ አንዳንዶቹ ይሀውም ሽማግሌዎች እና ከዒልም የራቁ ሰዎች ደግሞ አሁንም ድረስ ከእነሱ ጋር የሙጥኝ እንዳሉ ነው። የተከበሩ ሸይኻችን ይህንን በተመለከተ እውነታውን ግልፅ ቢያደርጉልን። መልስ፡- እነዚህና መሰሎቻቸው የተወገዘን ነገር የሚፈፅሙና ውዳቂ ተግባርንም የሚዳፈሩ የሱፊዮች ጭፍራ ናቸው።

ከዛም ባሻገር ነብዩ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ በማለት ከተናገሩባቸው የሟርተኞች ጎራም የሚሰለፉ ናቸው። (ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ስለ አንዳች ነገር የጠየቀ ሶላቱ ለአርባ ሌሊቶች ተቀባይነት የለውም።) ይህም የሆነበት ምክንያት የሩቅ ምስጢር እናውቃለን ብለው በመሞገታቸው፣ የጂኖች አገልጋይም በመሆናቸው፣ እነርሱንም በማምለካቸው፣ እያድበሰበሱ በሚሠሩት አላህ በሙሳ እና ፊርዓውን ታሪክ ላይ እንዲህ ያለበትን የድግምት ስራ እየሰሩ ሰዎችንም የሚያታልሉ በመሆናቸው ነው፡- {«ጣሉ» አላቸው። (ገመዶቻቸውን) በጣሉም ጊዜ የሰዎቹን ዓይኖች ደገሙባቸው፡፡ አስፈራሩዋቸውም፡፡ ትልቅ

[1] እነዚህ ጥያቄዎች እና መልሶች -ኑሩን ዐለ ደርብ- ከተሰኘ ፕሮግራም የተወሰዱ ናቸው።

ድግምትንም አመጡ።}[1]ስለዚህም ከዚህ የተከበሩው ሐዲሥ እና ከተከታዩ የነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ቃል በመነሳት ወደ እነርሱ መሄድም ይሁን እነርሱን መጠየቅ የሚፈቀድ አይደለም፡- (ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ሟርተኛው የተናገረውን ያመነ ሰው ወደ ሙሐመድ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን- በተወረደው ክዷል።) በሌላ ቃል ደግሞ፡- (ሟርተኛ ወይም ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ጠንቋዩ የተናገረውን ያመነ ወደ ሙሐመድ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በተወረደው ክዷል።)

ከአላህ ውጭ ያለን አካል መማጸናቸው እና ከአላህ ውጭ ባለ አካልም የጭንቅ ገላጋይ አድርገው መያዛቸው፤ አልያም አያቶቻቸው እና ቅድመ አያቶቻቸው በፍጥረተ ዓለሙ ላይ ተፅእኖ የመፍጠር ድርሻ እንዳላቸውም ይሁን ህሙማንን እንደሚፈውሱ አልያም ሩቅ ከመሆናቸውና ወይም ሙታን ከመሆናቸውም ጋር ለሚማፀን ምላሽ መስጠት እንደሚችሉ መሞገታቸው ከከባዱ ሽርክ እና ከኩፍር የሚመደብ ነው። በመሆኑም እነርሱን በተመለከተ ተገቢው ነገር ወደነርሱ አለመሄድ እነርሱንም አለመጠየቅ ቢናገሩም አለማመን ነው። ምክንያቱም በዚህ ድርጊታቸው የጠንቋዮችና የደጋሚዎችን ስራ ከአላህ ውጭ ያለን አካል የሚያመልኩት፣ ከአላህ ውጭ ባለ አካል ከጭንቅ መገላገልን ከጃዮች፣ ከአላህ ውጭ ባለ ጂንም ይሁን ሙታን አልያም ሌሎች አባቶቻችን አያቶቻችን እያሉ አልያም ሌሎች ወልይና ባለ ከራማ አድርገው ራሳቸውን የሚያስጠጉባቸው አካላት እርዳታን ከጃይ የሆኑትን ሙሽሪኮችን ስራ አቅፈው የያዙ ናቸው። ይልቁን ይህ ሁሉ ድርጊት የድግምት እና በንፁሁ ሸሪዓም የተወገዘ የሟርትና የጥንቆላ ስራ ነው።

ይህ የሚያደርጉት የተወገዘው እና በስለታማ ነገር ራሳቸውን እየወጉ አልያም ምላሳቸውን እየቆረጡ የሚያሳዩት ነገርን በተመለከተ መታወቅ ያለበት ጉዳይ አስመስሎ የማሳየት ጉዳይ እንደሆነ ነው። ይህ ሁሉ ቀደም ብለንም እንዳሳለፍነው ቁርአናዊና ሐዲሣዊ ማስረጃዎች ሐራም ያደረጉትና ከርሱም ያስጠነቀቁበት የሆነው የሲሕር ድርጊት ነው። በመሆኑም የትኛውም ጤናማ አእምሮ ያለው ሰው በዚህ ሊታለል አይገባውም። ይህ ደግሞ ጥራት የተገባው የላቀው አላህ እንዲህ ሲል ከተናገረበት የፊርዓውን ደጋሚዎች ዓይነት የሚካተት ነው፡-

{يخيّل إليه من سحرهم أنها تسعى}

[1] ሱረቱ አል-አዕራፍ አንቀፅ ቁጥር፡ 116

{ከድግምታቸው የተነሳ እነርሱ የሚሮጡ (እባቦች) ሆነው ወደርሱ ተመለሱ።}[1]እነዚህ ድግምትን እና ሟርትን፣ ጥንቆላን ከአላህ ውጭ ባለ አካል መታገዝን፣ ከአላህ ውጭ ባለ አካል የጭንቅ ገላጋይ በማድረግ ከአላህ ጋር ማጋራትን የሩቅ ምስጢርን አውቃለሁ የሚል ሙግትን በፍጥረተ አለሙ ማስተናበርንም ከመሞገት ጋር አብረው የሰበሰቡ ሰዎች ናቸው።

እነዚህ ድርጊቶች ደግሞ የተለያዩ የከባዱ ሽርክ እና የግልፅ ክህደት አይነቶች፤ አላህ ሐራም ያደረገው የድግምት ደርጊት ከአላህ ውጭ ማንም የማያውቀውን የሩቅ ምስጢርን አውቃለሁ የሚል ሙግት ዓይነቶች ናቸው። ጥራት የተገባው አላህ እንዲህ እንዳለን ማለት ነው፡-

{قل لا يعلم من في السموات والأرض الغيب إلا الله}

{«በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ ሩቅን ምስጢር አያውቅም። ግን አላህ (ያውቀዋል)። መቼ እንደሚቀሰቀሱም አያውቁም» በላቸው።}[2] ሁኔታቸውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሙስሊም ሁሉ እነርሱን ማውገዝ፣ ክፉ እንቅስቃሴያቸውንም ግልፅ ማድረግና ጉዳያቸውንም ለሚመለከተው አካል ማመልከት ይገባል።

በሙስሊሞች ሀገር ከሆኑ ክፋታቸውን ለማቀብ እና ሙስሊሞችን ከውሸታቸውና ከአታላይነታቸው ለመታደግ ሲባል ሸሪዓውን በጠበቀ መልኩ የሚገባቸውን ቅጣት እንዲቀጡ ጉዳያቸውን ለሚመለከተው አካል ማመልከት ይገባል።

አላህ ይወፍቀን (ለመልካሙ ይግጠመን)

## ጂን በሚጠቀም የህዝብ ሐኪም የሚደረግ ሕክምና

ጥያቄ፡- እንደሚባለው ከሆነ በሕዝብ መድኃኒት የሚያክሙ ሰዎች አሉና ወደ ተባሉት ሰዎች ስሄድ እንዲህ አለኝ፡- “ስምህን እና የእናትህን ስም ጻፍና ነገ ትመጣለህ” ከዚያም የሆነ ሰው ወደነርሱ ሲመጣ “አንተ ጉዳይህ እንዲህ እንዲህ አይነት ነው፤ መፍትሄው ደግሞ እንዲህ ብታደርግ ነው” ይሉታል። ከመካከላቸውም የሚያክመው በቁርአን እንደሆነ የሚሞግትም አለ። ታዲያ እንደዚህ አይነት ሰዎችን በተመለከተ ምን ይሉናል? ወደ እነርሱ መሄድስ ኢስላማዊ ፍርዱ ምንድን ነው?

---

[1] ሱረቱ ጧሀ አንቀፅ ቁጥር፡ 66

[2] ሱረቱ አን-ነምል አንቀፅ ቁጥር፡ 65

መልስ፡- በህክምናው ይህንን ዓይነቱን የፈውስ ሂደት የሚከተል ሰው የሚታከመው በአጋንንቶች እንደሆነ እና የሩቅ ምስጢርንም እንደሚሞግት አመላካች ነው። ስለዚህም እንደዚህ አይነቱ ሰው ዘንድ መተካከም አይፈቀድም፤ ልክ ወደ እሱ መሄዱም ሆነ መጠየቁ እንደማይፈቀደው ሁሉ ማለት ነው። ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋልና፡- (ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ስለ አንዳች ነገር የጠየቀ ሶላቱ ለአርባ ሌሊቶች ተቀባይነት የለውም።) ሙስሊም በሶሒሐቸው ዘግበውታል ወደ ጠንቋዮች፣ ሟርተኞች እና ድግምተኞች መሄድም ይሁን እነርሱን መጠየቅ እና የሚሉትንም አምኖ መቀበል መከልከላቸው በበርካታ ሐዲሦች ተረጋግጧል። ነቢዩ -የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህም ብለዋል፡- (ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ሟርተኛው የተናገረውን ያመነ ሰው ወደ ሙሐመድ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን- በተወረደው ክዷል።) የሩቁን ነገር ዐውቆታል የሚል ሁሉ፤ ጠጠር በመወርወር ወይም በማስቀመጥ፤ መሬት ላይ በማስመር፤ በሽተኛውን ስሙንና የእናቱን ስም ወይም የዘመዶቹን ስም በመጠየቅ የሩቁን ምስጢር አውቃለሁ የሚል ሁሉ ይህ ድርጊቱ ሰውዮው ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እነርሱን ከመጠየቅም ይሁን የሚሉትን አምኖ ከመቀበል ከከለከሉን ጠንቋዮችና ሟርተኞች አንዱ መሆኑን አመላካች ነው።

በመሆኑም እነርሱ በቁርኣን ነው የምናክመው ብለው ቢሞግቱም እነርሱን ከመጠየቅም እነርሱ ዘንድ ከመታከምም መጠንቀቅ ይገባል። ምክንያቱም የውሸት ሰዎች ማታለልና ማጭበርበር ልማዳቸው ስለሆነ የሚናገሩትን የትኛውንም ነገር ሊታመኑ አይገባቸውም። ስለዚህም ማንኛውም እነርሱን የሚያውቅ ሁሉ የአላህን ፍርድ እንዲያሰፍኑባቸው እና ሙስሊሞችም ከክፋታቸውም ከጥፋታቸውም ያላግባብ ከሚበዘብዙትም ገንዘብ ይድኑ ዘንድ ጉዳያቸውን በሀገሩ ለሚገኙ ዳኞች፣ ባለስልጣናት እና ፍርድቤት አሳልፈው ሊሰጧቸው ይገባል።

ረዳታችንም አላህ ነው፤ ከአላህም ውጬ ኃይልም ብልሀትም የለም።

## የድግምት ሸሪዓዊ ፈውስ[1]

ጥያቄ፡- ከትላልቅ ሰዎች አንዱ "ድግምት ተሰርቶብኛል ብሎ የሚያስብ ሰው ሰባት የቁርቁራ ዛፍ ቅጠል ይውሰድና ከዚያም በባልዲ ውሃ ውስጥ ነክሮ ሁለቱን "ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ" እና

[1] ከ "ኑሩን ዐለ ደርብ" ካሴት ቁጥር 53 የተወሰደ

"ቁል አዑዙ ቢረቢናስ" እንዲሁም "አየተል ኩርሲይን"፤ 'ቁል ያአዩሃል ካፊሩን'፤ እንዲህ የሚለውም አንቀፅ 'ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር 102' እና ሱረቱል ፋቲሐን ይቅራ" ሲል ሰምቻለሁ፡- ይህ አባባሉ ትክክለኛነቱ ምን ያክል ነው? ድግምት ተሰርቶብኛል ብሎ የሚያስብ ሰውስ ምንድን ነው ማድረግ ያለበት? ያግዙን አላህ ያግዞትና

መልስ፡- ድግምት ያለ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ነው። አንዳንዱ ግን መስሎ መታየት ብቻ እንጅ እውነትነት የለውም። የሚከሰት እና ጥራት የተገባው የላቀው አላህም እንዲህ ብሎ እንደነገረን ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችለው ግን በአላህ ፈቃድ ነው፡-

{واتبعوا ما تتلوا الشياطين على ملك سليمان وما كفر سليمان ولكن الشياطين كفروا يعلمون الناس السحر وما أنزل على الملكين ببابل هاروت وماروت وما يعلمان من أحد حتى يقولا إنما نحن فتنة فلا تكفر فيتعلمون منهما ما يفرقون به بين المرء وزوجه وما هم بضارين به من أحد إلا بإذن الله}

{ሰይጣናትም በሱለይማን (ሰሎሞን) ዘመነ መንግስት የሚያነቡትን (ድግምት) ተከተሉ። ሱለይማንም አልካደም፤ (ድግምተኛ አልነበረም)፤ ግን ሰይጣናት ሰዎችን ድግምትን የሚያስተምሩ ሲኾኑ ካዱ። ያንንም በባቢል በሁለቱ መላእክት በሃሩትና ማሩት ላይ የተወረደውን ነገር (ያስተምሩዋቸዋል)። «እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም። ከእነሱም በሰውየውና በሚስቱ መካከል በርሱ የሚለዩበትን ነገር ይማራሉ። እነርሱም በአላህ ፈቃድ ካልኾነ በርሱ አንድንም ጎጂዎች አይደሉም።} ማለትም: ሁለቱ መላዕክት {«እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም። ከእነሱም በሰውየውና በሚስቱ መካከል በርሱ የሚለዩበትን ነገር ይማራሉ። እነርሱም በአላህ ፈቃድ ካልሆነ በርሱ አንድንም ጎጂዎች አይደሉም።}[1]በመሆኑም ድግምትም ተፅዕኖ ያሳድራል ነገር ግን ይሁንታዊ በሆነው የአላህ ፈቃድ ነው። ምክንያቱም የትኛውም ነገር ጥራት በተገባው የላቀው አላህ ፈቃድ ኖሮት ካልሆነ በቀር የሚሆን የለምና። በእውነቱ ይህ ድግምት የራሱ መድኃኒት እና ፈውስ አለው። በነቢዩ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን - ላይም ተከስቶ የነበረና አላህ እርሳቸውን ከዛው ያዳነበትና ከክፋቱም የታደገበት፤ ደጋሚው የሠራውም ተገኝቶ እንዲከሽፍ በማድረግ አላህ ነብዩን የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ያዳነበት ጉዳይ ነው። ልክ እንደዚሁ ሟርተኛው የቋጠረው ቋጠሮ ወይም ያቆላለፈው ችንካር አልያም ሌላ ድግምቱን የሰራበት ነገር ተገኝቶ ማፍረስ የሚቻል ከሆነ ድግምቱን ያከሽፈዋል።

[1] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር 102

ምክንያቱም አላማቸው ሊሳካም ሊከሽፍም የሚችል ከመሆኑም ጋር እነርሱ እኩይ ስራቸውን ሲሰሩ በቋጠሮው ላይ እየተፉ የሚሰሩ መሆናቸው የታወቀ ነገር ነውና።

ጥራት የተገባው የላቀው አምላካችን አላህ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው። ድግምቱ አንዳንዴ ቁርአን በመቅራትም ይፈወሳል። የሚቀራው ህመምተኛው ጤናማ አእምሮው ኖሮት ራሱ ሊሆንም ይችላል ወይም ሌላ ሰው ቱፍታ እያደረገ በደረቱም በሌላ የሰውነት አካሉም እያሸ ሊቀራለትም ይችላል። የሚቀሩት የቁርአን አንቀፆች፡- አል-ፋቲሐ፣ አየተል ኩርሲይ፣ "ቁል ሁወሏሁ አሐድ"፣ "ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ" እና "ቁል አዑዙ ቢረቢናስ" ፤ የታወቁት ሲሕርን የተመለከቱ የሱረቱ አል-አዕራፍ ፣ የሱረቱ ዩኑስ እና የሱረቱ ጣሃ አንቀፆችን መቅራት ይችላል።

ከሱረቱል አዕራፍ ደግሞ ተከታዩ የአላህ ቃል፡-

{وأوحينا إلى موسى أن ألق عصاك فإذا هي تلقف ما يأفكون. فوقع الحق وبطل ما كانوا يعملون. فغلبوا هنالك وانقلبوا صاغرين}

{ወደ ሙሳም፡- «በትርህን ጣል» ስንል ላክን። (ጣላትም) ወዲያውኑም የሚቀጣጥፉትን (ማታለያ) ትውጣለች። እውነቱም ተገለጸ። ይሠሩት የነበሩትም (ድግምት) ተበላሸ። እዚያ ዘንድ ተሸነፉም። ወራዶችም ሆነው ተመለሱ።}[1]ከሱረቱ ዩኑስ ተከታዩ የአላህ ቃል፡-

{وقال فرعون ائتوني بكل ساحر عليم. فلما جاء السحرة قال لهم موسى ألقوا ما أنتم ملقون. فلما ألقوا قال موسى ما جئتم به السحر إن الله سيبطله إن الله لا يصلح عمل المفسدين. ويحق الله الحق بكلماته ولو كره المجرمون}

{ፈርዖንም፡- «ዐዋቂ ድግምተኛን ሁሉ አምጡልኝ» አለ። ድግምተኞቹም በመጡ ጊዜ ሙሳ ለእነርሱ፡- «እናንተ የምትጥሉትን ነገር ጣሉ» አላቸው። (ገመዶቻቸውን) በጣሉም ጊዜ ሙሳ አለ፡- «ያ በርሱ የመጣችሁበት ነገር ድግምት ነው። አላህ በእርግጥ ያፈርሰዋል። አላህ የአጥፊዎችን ሥራ ፈጽሞ አያበጅምና።» አላህም ከሐዲዎች ቢጠሉም እውነትን በቃላቱ ያረጋግጣል።}[2]ከሱረቱ ጧሀ ተከታዩ የአላህ ቃል:

{قالوا يا موسى إما أن تلقي وإما أن نكون أول من ألقى. قال بل ألقوا فإذا حبالهم وعصيهم يخيل إليه من سحرهم أنها تسعى. فأوجس في نفسه خيفة موسى. قلنا لا تخف إنك أنت الأعلى. وألق ما في يمينك تلقف ما

---

[1] ሱረቱ አል-አዕራፍ አንቀፅ ቁጥር፡ 117-119

[2] ሱረቱ ዩኑስ አንቀፅ ቁጥር፡ 79-82

صنعوا إنما صنعوا كيد ساحر ولا يفلح الساحر حيث أتى}

{«ሙሳ ሆይ! ወይ ትጥላለህ ወይም በመጀመሪያ የምንጥል እንኾናለን» (ምረጥ) አሉ። «አይደለም ጣሉ» አላቸው። ወዲያውም ገመዶቻቸውና ዘንጎቻቸው ከድግምታቸው የተነሳ እነርሱ የሚሮጡ (እባቦች) ኾነው ወደርሱ ተመለሱ። ሙሳም በነፍሱ ውስጥ ፍርሃትን አሳደረ። «አትፍራ አንተ የበላዩ አንተ ነህና» አልነው። «በቀኝ እጅህ ያለቸውንም በትር ጣል። ያንን የሠሩትን ትውጣለችና። ያ የሠሩት ሁሉ የድግምተኛ ተንኮል ነውና።

ድግምተኛም በመጣበት ስፍራ ሁሉ አይቀናውም» (አልን)።}[1]እንዲሁም {ቁል ያ አዩሃል ካፊሩን}፣ {ቁል ሁወሏሁ አሐድ}፣ {ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ}፣ {ቁል አዑዙ ቢረቢናስ} ምዕራፎችን አሟልቶ ይቀራል። {ቁል ሁወሏሁ አሐድ}፣ {ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ}፣ {ቁል አዑዙ ቢረቢናስ} እነኝህ ሶስቱን እያንዳንዳቸውን ሶስት ጊዜ እየደጋገመ ቢቀራ የተሻለ ነው። ከዚያም አላህ እንዲፈውሰው እንዲህ በማለት ዱዓ ያድርግ: "አሏሁ ረበ-ን-ናስ አዝሂቢል ባእስ ወሽፊ አንተ-ሽ-ሻፊ ላ ሺፋአ ኢላ ሺፋኡክ ሺፋአን ላዩጋዲሩ ሰቀማ" ሶስት ጊዜ ደጋግሞ ይበል። (ትርጉሙም: አላህ ሆይ! የሰው ልጆች ጌታ የሆንከው! ከአንተም ውጭ ፈውስ የለም ፈዋሹም አንተው ነህና ህመሙን አስወግደህ ምንም አይነት እንከን የማያስቀር ፈውስህን ለግስ።) እንዲህም በማለት ሩቃውን ይቀጥል፡- "ቢስሚላሂ አርቂክ ሚን ኩሊ ሸይኢን ዩእዚክ ወሚን ሸሪ ኩሊ ነፍሲን አው ዓይኒን ሐሲዲን አሏሁ የሽፊክ ቢስሚላሂ አርቂክ" ሶስት ጊዜ ደጋግሞ ይበል። (ትርጉሙ፡- ከሚጎዳህ ነገር ሁሉ፣ ከክፉ ነፍስም ይሁን ከምቀኛ ዓይን አላህ ይፈውስህ ዘንድ በአላህ ስም አክምሀለሁ፤ በአላህ ስም አክምሃለሁ) በተጨማሪ በሩቃው እንዲህም ካለ፡- "አዑዙ ቢከሊማቲላሂ ታማህ ሚን ሸሪ ማ ኸለቅ" የተሻለ ይሆንለታል። (ትርጉሙም፡- ከፍጡራኑ ክፋት ምሉእ በሆነው የአላህ ቃል እጠበቃለሁ።)

ይህ ሁሉ እጅግ ጠቃሚ የሆነ መተካከሚያ ዘዴ ነው። ይህንኑ የሩቃ እና ዱዓእ ሂደትን ተከትሎ ውኃ ውስጥ በመቅራት ድግምቱ የተሰራበት ሰው ቢጠጣው ቀሪውን ደግሞ ቢታጠብበት በአላህ ፈውስና መድሀኒቱን ሊያስገኝለት የሚችል ዘዴ ነው። ሰባት የአረንጓዴ ቁርቁራ ዛፍ ቅጠሎችን ጨፍጭፎ በውኃ ውስጥ ቢጨምረው ይህም እንዲሁ ፈውሱን የሚያስገኝለት ዘዴ ነው። ይህ ደግሞ ብዙዎች የሞከሩት አላህም ለብዙዎቹ ሰበብ ያደረገላቸው ነገር ነው። ብዙ ሰዎችንም እንዲህ አድርገንላቸው አላህ ፈውስ አደርጎላቸው ያየንበትም ነው።

---

[1] ሱረቱ ጣሀ አንቀፅ ቁጥር፡ 65-69

በመሆኑም ድግምት ተሰራብኝ ብሎ ለሚያስብ ሁሉ ፋይዳው የጎላ ፈውስ ይሆንለታል። ይህ መድሃኒት በድምግት ስንፈተ ወሲብ ላጋጠመው ሰውም የሚሆን ነው። ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች ከሚስታቸው ጋር ግንኙነት መፈፀም ባለመቻላቸው ይህንን ሩቅያና ዱዓ ከተጠቀሙበት በኃላ መድሀኒቱ ሆኖ እያገኘው ስለሆነ ነው። ሩቃውን ራሱም ይሁን ሌላ ሰው ውኃ ላይ ከቀራ በኃላ የሚጠጣውን ጠጥቶ በቀሪው ቢታጠብበት ድግምት ተሰራብኝ ለሚልም ይሁን ግንኙነት መፈፀም ላልቻለ ሁሉ በአላህ ፈቃድ ፈውስ ሆኖ እንደሚያገኘው ነው። እነዚህ ለፈውስ እንደሰበብ ናቸው፤ ፈውስ የሚለግሰው ጥራት የተገባው የላቀው አምላካችን አላህ ብቻ ነው። እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ፤ ህመሙም ይሁን ፈውሱም በእጁ ነው፤ ጥራት ይገባውና ሁሉም ነገርም በአላህ ውሳኔና ፍርድ የሚሆን ነው፤ የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ማለታቸውም በሶሒሕ ሐዲሥ ተረጋግጧል፡- (የሚያውቅ አውቆት የማያውቅ አላወቀውም እንጅ አላህ የትኛውንም በሽታ ሲያወርድ ከመድኃኒቱ ጋር ነው። )

ይህም ጥራት ከተገባው የላቀው አላህ ችሮታ ሲሆን ወደቀናው መንገድ የሚመራውም የሚያመላከተውም ተውፊቁንም የሚገሰጠው እርሱ ነው።

## ጂኒ በሰው አካል ውስጥ የሚገባ ስለመሆኑ እውነታውን ግልጽ ማድረግ እና ያንን ላስተባበሉ ሰዎች ምላሹን መስጠት[1]

ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ሰላትና ሰላምም በአላህ መልእክተኛ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው እንዲሁም የእርሳቸውን ቅን ጎዳና በተከተለም ላይ ሁሉ ይስፈን።

በመቀጠል: አንዳንድ የሀገር ውስጥ ጋዜጦች እና ሌሎችም በዚህ አመት ማለትም በ1407 ዓመተ ሂጅራ በወርሀ ሸዕባን በአንዲት ሪያድ ያለች እህታችን ላይ ሰፍኖ የነበረ ጂኒ ነዋሪነቱ ሪያድ የሆነው ዐብደላህ ቢን ሙሸሪፍ አል-ዓምሪይ ዘንድ እስልምናውን ከተቀበለ በኃላ እኔው ዘንድ በይፋ እስልምና ስለመቀበሉ አጫጭር እና ረዣዥም ሀተታዎችን አስተላልፈዋል። ይህም የሆነው ቀደም ብለን ያወሳነው ወንድማችን በህመምተኛዋ ቁርአን ቀርቶላት ጂኒውንም እያናገረ በአላህም ገሰፆ በደልም ከባድ ወንጀል እያሳወቀ ዳዕዋ ካደረገለት በኃላ ነው። ጂኒውም

---

[1] ለሸኽ ዐሊይ አጥ-ጠንጣዊይ በ 3/11/1408 ሂጅራ የተሰጠ ምላሽ

ሃይማኖቱ ቡድሂስት ካፊር መሆኑንም ባሳወቀው ጊዜ ወደ ኢስላም ጥሪ አድርጎለት ከልጅቲቱም እንዲወጣ ባሳሰበው ጊዜ ጂኒው ዳዕዋውን ሰምቶ ነው ዐብደሏህ ዘንድ እስልምናን የተቀበለው። ከዚያም ዐብደላህም የሴቲቱ ቤተሰቦችም ልጅቱ እኔ ዘንድ ሆና ጂኒው እስልምናን ሲቀበል እንድሰማ ፈለጉና እኔው ዘንድ መጥተው ጂኒውን ወደ ልጂቱ የገባበትን ምክንያት ጠይቄው በእርሷ ምላስ ቢናገረውም አነጋገሩ የወንድ ልጅ እንጅ የሴት ልጅ ባልሆነ አንደበት ምክንያቶቹን ነገረኝ።

ይህ ሲሆን እርሷ በአጠገቢ ባለው ወንበር ነበር የተቀመጠቸው። ወንድምና እህቶቿ እና ቀደም ብለን ያወሳነው ዐብደላህ ቢን ሙሽሪፍ እንዲሁም የተወሰኑ ሌሎች ሰዎችም ሲታዘቡ ነበር። እስልምናን በይፋ የተቀበለ ሲሆን ህንዳዊ እና የቡድሂስት ሃይማኖት ተከታይም እንደነበር ተናግሯል። በመሆኑም አላህን እንዲፈራ፣ ከልጂቱም እንዲወጣና እርሷንም ከመበደል እንዲታቀብ ገሠፅኩት። እርሱም እንዲህ በማለት መለሰልኝ፡- "እኔ በእስልምና እርግጠኛ ሆኛለሁኝ" እኔም አላህ እርሱን እንደመራው ሌሎችም ወደቀናው ጎዳና ሊመሩ ዘንድ ህዝቦቹን ወደ እስልምና ጥሪ እንዲያደርግላቸው አደራ ብየው ተስማምቶ ወዲያውኑ ልጂቱን ለቋታል። የመጨረሻ ቃሉም "አሰላሙ ዓለይኩም" የሚል ነበር።

ከዚያም ሴቲቱ በተለመደው አንደበቷ መናገር ጀመረች፤ ከድካሙም ነፃ መውጣቷንና እረፍት እየተሰማት እንደሆነም ተናገረች። ከዚያም ከወር ወይም ከዚያ በላይ ከቆየች በኋላ ከሁለት ወንድሞቿ፣ አጎቷ እና እህቷ ጋር ሆነው ተመልሳ ወደ እኔ መጣች፣ እናም ደህና እንደሆነች እና ከዛ በኃላም ተምልሶባት እንደማያውቅ ተናገረች። ወልሐምዱሊላህ። ጂኒው በነበረባት ወቅት የሚሰማት ስሜት ምን እንደነበር ጠየቅኳት፤ እሷም "ከሸሪዓው ጋር የሚቃረኑ መጥፎ ሐሳቦች ይሰማት እንደነበርና ወደ ቡድሂስት ሃይማኖትም እንዲሁም በቡድሂስት በኩል ወደተፃፉ መፃህፍቶችም ለማሰስ ዝንባሌ ያድርባትም እንደነበር ተናገረች።

ከዚያም አላህ ካዳናት በኋላ እነዚህ መጥፎ ሃሳቦች ከእርሷ ተወግደው እርሷም ወደ ቀድሞው ከእነዚህ ጋጠወጥ ሃሳቦች ነፃ ወደ ሆነው ሃሳቧ መመለስ ችላለች። የተከበሩ ሸኽ ዐሊይ አጠንጧዊይ እንዲህ አይነቱ ጉዳይ መከሰቱን እንዳስተባበሉ እና ማታለል እና ውሸትም እንደሆነ እና ሴትየዋ በውስጧ አምቃ የያዘችው ተቀርፆ የቀረ የቃላት ክምችት ብቻ እንደሆነ ገልፀዋል የሚል መረጃ ደርሶኛል። እንዲህ ያለበትን የተቀረፀበት ካሴት አጠያይቄ እንደዛ ማለታቸውን ደርሸበታለሁ። ይህ ግን እጅጉን ገርሞኛል! ጂኒውን በርካታ ጥያቄዎች እየጠየቅኩት እየመለሰልኝ እንዴት ተቀርፆ የነበረ ቃላት ብቻ ነው ሊባል ይችላል?! ይህ አስቀያሚ ስህተት ከመሆኑም ባሻገር እንቶፈንቶ እውን ይሆናል እንደማለትም ነው። ከዛም አልፎ ጂኒ በሰው ልጅ በኩል ሊሰልም ይችላል የሚለውን ነገር ከተከታዩ የአላህ ቃል ጋር እንደሚጋጭ አድርገውም ቆጥረውታል፡-

{وهب لي ملكاً لاينبغي لأحد من بعدي}

{«ጌታዬ ሆይ! ለእኔ ማር። ከእኔ በኋላ ለአንድም የማይገባንም ንግሥና ስጠኝ። አንተ ለጋሱ አንተ ብቻ ነህና»} ይህም ቢሆን አላህ ይምራውና ሌላኛው ስህተትና የተሳሳተ ግንዛቤም ነው። ጂኒ በሰው እጅ በኩል እስልምናን መቀበሉ የነብዩሏህ ሱለይማን ዱዓእ ጋር የሚጋጭ ምንም አይነት ነገር የለውም። በነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በኩል በርካታ ቁጥር ያላቸው ጂኖች እስልምናን ተቀብለዋል።

ይህም አላህ በሱረቱል አሕቃፍ እና በሱረቱል ጂን ላይ በግልፅ አስፍሮታል። በሁለቱ የሶሒሕ ኪታቦችም ከአቡ ሁረይራ ረዲየላሁ ዐንሁ በተላለፈ ሐዲሥ ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡- (ሰይጣን ከፊት ለፊቴ ቀርቦ ሶላቴን ሊያቋርጥብኝ ሞከረ ነገር ግን አላህ በእርሱ ላይ አቅምን ሰጠኝና አነቅሁት። በርግጥ ነግቶ እስክትመለከቱ ድረስ ከመስጂዱ ምሰሶዎች መካከል በአንዱ ላስረው አሰብኩና ድንገት "ጌታዬ ሆይ! ከእኔ በኋላ ለማንም የማይገባውን ንግሥና ስጠኝ።" የሚለው የወንድሜ ሱለይማን ዐለይሂ ሰላምን ዱዓእ አስታውሸ ተውኩት።)

{رب اغفر لي وهب لي ملكاً لا ينبغي لأحد من بعدي}

{«ጌታዬ ሆይ! ለእኔ ማር። ከእኔ በኋላ ለአንድም የማይገባንም ንግሥና ስጠኝ። አንተ ለጋሱ አንተ ብቻ ነህና»}[1]ከዚያም አላህ (ሰይጣንን) ተዋረዶ እንዲመለስ አደረገው።) ይህ የቡኻሪ ቃል ሲሆን የሙስሊም ዘገባ ቃል ደግሞ፡- (ትላንት ሌሊት ሶላት ላይ እያለሁ ከጂኖች መካከል የሆነ ክፉ ሶላቴን ሊያቋርጥብኝ ሲሽሎኮሎክ ነበር። ነገር ግን አላህ በእርሱ ላይ አቅም ሰጠኝና ቀፍድጄ ያዝኩት። በርግጥ ነግቶ ሁላችሁም ትመለከቱት ዘንድ ከመስጂዱ ምሰሶዎች መካከል በአንዱ ላስረው አሰብኩና ድንገት ተከታዩን የወንድሜ ሱለይማን ዓለይሂ ሰላምን ዱዓእ አስታውሸ ተውኩት፡-

{رب اغفر لي وهب لي ملكاً لا ينبغي لأحد من بعدي}

{«ጌታዬ ሆይ! ለእኔ ማር። ከእኔ በኋላ ለአንድም የማይገባንም ንግሥና ስጠኝ። አንተ ለጋሱ አንተ ብቻ ነህና»}[2]ከዚያም አላህ (ሰይጣንን) ተዋረዶ እንዲመለስ አደረገው።)

በቡኻሪይ ሸርጥ መሰረት አን-ነሳኢይ ከእናታችን ዓኢሻ (ረዲየላሁ ዐንሃ) እንደዘገቡት ነብዩ የአላህ

---

[1] ሱረቱ ሷድ አንቀፅ ቁጥር፡ 35

[2] ሱረቱ ሷድ አንቀፅ ቁጥር፡ 35

ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሲሰግዱ በነበረበት ወቅት ሰይጣን ወደ እርሳቸው መጣ። ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ቀፍድደው ያዙት፤ ከዚያም የአላህ መልእክተኛም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፡- (የምላሱን ለሀጭ እጄ ላይ እስኪሰማኝ ድረስ ቀፈደድኩት፤ የሱለይማን ዱዓእ ባይኖር ኖሮ ሰዎች ሊያዩት ዘንድ ታስሮ ያድር ነበር።) አሕመድና አቡ ዳውድ ከአቡ ሰዒድ የዘገቡት ሐዲሥ ሲሆን እንዲህ የሚል አለው፡- (ዘልየ አነቅኩት፤ የለሀጩ እርጥበት በነዚህ ሁለት ጣቶቼ በአውራ ጣቴ እና በጠቋሚ ጣቴ እስኪሰማኝ ድረስ አንቄ ከመያዝ ወደኋላ አላልኩም።) አል-ቡኻሪ በሶሒሐቸው ላይ ቅጽ 4 ገጽ 487 ከአል-ፈትሕ ከአቡ ሁረይራ ረዲየላሁ ዐንሁ በተላለፈ ሐዲሥም እንዲህ ብለዋል፡- የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የረመዳንን ዘካ በተመለከተ ኋላፊነት ሰጥተውኝ በነበረበት አጋጣሚ ድንገት አንዱ መጣና ዘግኖ ሊወስድ ሲል "ወሏሂ! ረሱል ዘንድ እንደማቀርብህ አስረግጠህ እወቅ!" ስለው “ችግረኛ ነኝ፤

በዛ ላይ የቤተሰብ ኋላፊነትም ስላለብኝ እጅግ በጣም አስፈልጎኝ ነው።” ሲለኝ ተውኩት። በማለዳው ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን “አባ ሁረይራ ሆይ! የትላንቱ እስረኛህ እንዴት ሆነ?” ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም መልሼ፣ “የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እርሱ ችግረኛ መሆኑንና የቤተሰብ ኋላፊነትም እንዳለበት ሲነግረኝ ጊዜ አሳዘነኝና ተውኩት" አልኳቸው። እርሳቸውም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን፡- "ዋሸቶሃል፤ ግን ተመልሶ ይመጣል።" አሉኝ። የአላህ መልእክተኛ ይመለሳል ስላሉኝ እኔም ተጠባበቅኩት። አሁንም በድጋሚ መጥቶ ከምግቡ ዘግኖ ሊወስድ ሲል በድጋሚ ያዝኩትና "ረሱል ዘንድ እንደማቀርብህ አስረግጠህ እወቅ!" ስለው “ችግረኛ ነኝ፤ በዛ ላይ የቤተሰብ ኋላፊነትም ስላለብኝ ነውና እባክህ ተወኝ? ድጋሚ ግን አልመለሰብህም።” ሲለኝ አሁንም ተውኩት። በማለዳው ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን “አባ ሁረይራ ሆይ! የትላንቱ እስረኛህ እንዴት ሆነ?” ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም መልሼ፣ “የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እርሱ በጣም ችግረኛ መሆኑንና የቤተሰብ ኋላፊነትም እንዳለበት ሲነግረኝ ጊዜ አሳዘነኝና ተውኩት" አልኳቸው። እርሳቸውም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን፡- "ዋሸቶሃል፤ ግን ተመልሶ ይመጣል።" አሉኝ። የአላህ መልእክተኛ ይመለሳል ስላሉኝ እኔም እንደገና መጠባበቄን ቀጠልኩ። አሁንም በድጋሚ መጥቶ ከምግቡ ዘግኖ ሊወስድ ሲል በድጋሚ ያዝኩትና፡- “አልመለስም እያልክ የተመላለስከው ይህ ሶስተኛ የመጨረሻ እድልህ ነውና ወደ ረሱል የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እወስድሀለሁ።" ስለው እንዲህ አለኝ፡ “አላህ አንተን የሚጠቅምበት ላስተምርህና ልቀቀኝ፡ ወደ መኝታህ በሄድክ ጊዜ አየተል ኩርሲይን (ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ 255) {አሏሁ ላ ኢላሃ ኢላ ሁወል ሐዩል ቀዩም ... } ሙሉ አንቀፁን ቅራ፤ ይህንን ካደረግክ እስኪነጋ ድረስ ሸይጧንም አይቀርብህም ከአላህም ጥበቃ ይደረግልሃል።" እኔም ለቀቅኩትና እንዲሄድ ፈቀድኩለት።

በማለዳም የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን “የትላንቱ እስረኛህ እንዴት ሆነ?” ሲሉኝ እኔም “አላህ እኔን የሚጥቅምበትን ቁምነገር እንደሚያስተምረኝ ብሎ የሆነ ነገር ተናገረና እኔም መንገዱን ክፍት አደረግኩለት” ስል መለስኩ። እርሳቸውም "ምን አይነት ነገር?" አሉኝ። እኔም “አላህ አንተን የሚጠቅምበት ላስተምርህና ልቀቀኝ፡ ወደ መኝታህ በሄድክ ጊዜ አየተል ኩርሲይን (ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ 255) {አሏሁ ላ ኢላሃ ኢላ ሁወል ሐዩል ቀዩም … } ሙሉ አንቀፁን ቅራ፤ ይህንን ካደረግክ እስኪነጋ ድረስ ሸይጧንም አይቀርብህም ከአላህም ጥበቃ ይደረግልሃል።" ለመልካም ነገር እጅግ ጉጉት የሚያድርባቸው ሰዎች ነበሩ። እርሳቸውም (እርሱ ውሸታም ቢሆንም የነገረህ ነገር ግን እውነት ነው። አባ ሁረይራ ሆይ! ባለፉት ሶስት ሌሊቶች ሲያወራህ የነበረው ማን እንደነበር ግን አውቀሃልን?) አሉኝ። "ኧረ አላወቅኩትም።" ስላቸው እርሳቸውም፡ (ሰይጣን ነው።) አሉኝ።[1]

ከሰፊያ ረዲየሏሁ ዓንሃ በተላለፈ እና ቡኻሪይና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሥ ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡- (“ሸይጧን በሰው ልጅ ውስጥ እንደ ደም ዝውውር ይሽከረከራል።”) ኢማሙ አሕመድ ደግሞ በአል-ሙስነድ ቅጽ 4 ገጽ 216 ላይ ሶሒሕ በሆነ ዘገባ እንዳስተላለፉት ዑሥማን ቢን አቢ ል-ዓስ ረዲየሏሁ ዓንሁ እንዲህ ብለዋል፡- “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ሰይጣን እኮ በእኔና በሶላቴ እንዲሁም በእኔና በቁርአኔ መካከል እየጋረደኝ ተቸገርኩ” አልኳቸው። እሳቸውም፡- ("ይህ ሰይጣን ሲሆን ኺንዚብ በመባል ይታወቃል። እንዲህ አይነቱ ስሜት ሲሰማህ "አዑዙቢላህ" በልና ሶስት ጊዜ ወደ ግራህ ትፉ።" አሉኝ። የተባልኩትንም ባደረግኩ ጊዜ አላህ ወስዋሱን አስወገደልኝ።) እንዲሁም ከነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በተላለፈ ሌሎች ሶሒሕ ሐዲሦችም እርሳቸውንም ጨምሮ እያንዳንዱ የሰው ልጅ የመላኢካ ቁራኛ እና የሸይጧን ቁራኛ እንዳለው ተናግረዋል።

ይሁን እንጅ በነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ላይ ያለው የሸይጧን ቁራኛ አላህ እርዳታውን ለግሷቸው ሰልሞ በኸይር ካልሆነ በቀር የማያዛቸው ሆኗል። ጂኒ ወደ ሰው ልጅ እንደሚገባና ሰይጣን ሰውን እንደሚመታም በቁርአንና በሐዲሥ እንዲሁም መላው ማህበረሰብም ሙሉ በሙሉ በሚስማማበት መልኩ ግልፅ እውነታ ሆኖ ሳለ እንዴት ወደ ዒልም የቀረበ ሰው ያለ እውቀትና ያለ ማስረጃ ይልቁን አንዳንድ አህሉሱና ወልጀማዓህን የሚቃረኑ ጠማማ አንጃዎችን በመከተል ብቻ እንዲህ አይነቱን እውነት ይስታል?! አሏሁል ሙስተዓ ወላ ሐውላ ወላ ቁወተ ኢላ

[1] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 255

ቢላህ! እናም ውድ አንባቢ ሆይ! እኔም እንግዲህ የአላህ ፈቃድ ከሆነ ይህንን አስመልክቶ የእውቀት ሰዎች የተናገሩትን ቃል እጠቅሳለሁ። ተከታዩን የአላህን ቃል በተመለከተ አላህ ይዘንላቸውና የተፍሲር ሊቃውንት ንግግር፡- {እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ብጤ እንጅ (ከመቃብራቸው) አይነሱም።}[1]

አቡ ጃዕፈር ቢን ጀሪር አላህ ይዘንላቸውና ስለ አንቀፁ ተፍሲር እንዲህ ብለዋል፡-

{الذين يأكلون الربا لا يقومون إلا كما يقوم الذي يتخبطه الشيطان من المس}

{እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ብጤ እንጅ (ከመቃብራቸው) አይነሱም።}[2]ያጣቀሱት እንዲህ ይላል፡- በዚህ ዓለም ሰይጣን ያንገዳግደዋል፤ ይተናነቀዋል ሰይጣንም እንደመታው ነው። (ከመንካቱ የተነሳ) ሲልም ከዕብደት የተነሳ ማለት ነው።

አል-በገዊይ አላህ ይዘንላቸውና ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ ተፍሲር ላይ እንዲህ ብለዋል፡-

{لا يقومون إلا كما يقوم الذي يتخبطه الشيطان من المس}

{እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ብጤ እንጅ (ከመቃብራቸው) አይነሱም።}[3]ማለትም እብደት ማለት ነው። እብድ ሲሆን "ነካ ያደርገዋል" ወይም "ንቅል" ይባላል። የሸይኹ ቃል እዚሁ ተቋጨ።

ኢብኑ ከሲር አላህ ይዘንላቸውና ከላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ ሲተረጉሙ እንዲህ ብለው አውስተዋል፡-

{الذين يأكلون الربا لا يقومون إلا كما يقوم الذي يتخبطه الشيطان من المس}

{እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ብጤ እንጅ (ከመቃብራቸው) አይነሱም።}[4]ማለትም፡- በእለተ ትንሣኤ

[1] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 275

[2] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 275

[3] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 275

[4] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 275

ከመቃብራቸው የሚነሱት የሚጥል በሽታ የያዘው ሰው የሚጥል በሽታው እያለበት ሲነሳ እንደሚንገዳገደው እየተንገዳገዱ ብቻ ነው። ይሀውም የሚነሳው በተዛባ አነሳስ በመሆኑ ነው። ኢብኑ አባስ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) እንዲህ ብለዋል፡- (ወለድ የሚበላ ሰው በእለተ ትንሳኤ ከመቃብሩ የሚነሳው እንደ እብድ እየተናነቀው ነው።) ኢብኑ አቢ ሐቲም ዘግበውታል፤ እንዲሁም ከሚከተሉትም ተላልፏል፡-

ከዐውፍ ቢን ማሊክ፣ ከሰዒድ ቢን ጁበይር፣ ከአሰ-ሱዲይ፣ ከአል-ረቢዕ ቢን አነስ፣ ከቀታዳህ እና ከሙቃቲል ቢን ሐያን ከመሳሰሉት ሁሉ ተላልፏል። አላህ ይዘንላቸውና ንግግራቸው እዚህ ጋር አበቃ።

አል-ቁርጡቢይም አላህ ይዘንላቸውና አንቀፁን ሲተነትኑ እንዲህ ብለዋል፡-

{الذين يأكلون الربا لا يقومون إلا كما يقوم الذي يتخبطه الشيطان من المس}

{እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ብጤ እንጅ (ከመቃብራቸው) አይነሱም።}[1]በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚጥል በሽታ ከጂኒዎች በኩል ሊከሰት እንደሚችል ያስተባበለ እና በዚሁ ጉዳይ የሚንገዳገዱት በተፈጥሯዊ ህመም ብቻ እንጅ ሰይጣን ወደ ሰው ልጅ የሚገባ አይደለም ሰይጣን መታው የሚባል ነገርም የለም የሚሉ ሰዎች አቋማቸው ውድቅ እንደሆነ እንረዳለን። በዚህ ረገድ የተፍሲር ሊቃውንት እጅግ ብዙ ብለዋል፡-

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ ረሒመሁላህ በመጅሙዕ አል-ፈታዋ ቅጽ 19 ገጽ 9 እስከ ገጽ 65 ላይ ("ኢዷሑ ደላላህ ፊ ዑሙሚ ሪሳላህ ሊሠቀለይን") በተሰኘው ኪታባቸው በንግግራቸው መሀል እንዲህ ብለዋል፡- "... ስለዚህም ነው ከሙዕተዚሊዮች እንደ ጁባኢይ እና አቢ በክር አር-ራዚ እንዲሁም ሌሎችም ጂኒ ሰይጣን በመታው ሰው ሊገባ መቻሉን ያወገዙት።

ምንም እንኳ በዚህ በኩል ስህተት ላይ ቢወድቁም የጂኖችን ህልውና ግን አላስተባበሉም። ጉዳዩ እንደ የጂኖች ህልውና ጉልህ ስላልሆነላቸው በጉዳዩ ስህተት ላይ ቢወድቁም። ስለዚህም ነው አሽዓሪይ የአህሉ ሱናህ ወልጀማዓን ቃል ሲጠቅስ ጂኒ ሰይጣን በመታው ሰው እንደሚገባም የጠቀሰው። ልክ የላቀው አላህ እንዲህ እንዳለን፡-

---

[1] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 275

{الذين يأكلون الربا لا يقومون إلا كما يقوم الذي يتخبطه الشيطان من المس}

{እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ብጤ እንጅ (ከመቃብራቸው) አይነሱም።}[1] ዐብደሏህ ቢን አሕመድ ቢን ሐንበል ለአባቱ፡- "አንዳንድ ሰዎች ጂኒ በሰው ልጅ አይገባም ይላሉ" አልኩት እርሱም እንዲህ አለኝ: "ልጄ ሆይ! እየቀጠፉ ነው። ሰይጣን በመታው ሰው አንደበት የሚናገሩት እኮ ሰይጣኖቹ ናቸው።" ይህ ደግሞ በቦታው ተገቢው ማብራርያ የተደረገበት ነው።

እንዲሁም አላህ ይዘንላቸውና በአል-ፈታዋ ቅጽ 24 ገፅ 276-277 ላይም እንዲህ ብለዋል፡- የጂን ህልውና በአላህ ኪታብና በመልዕክተኛው ሱና እንዲሁም ቀደምት ሰለፎችም አኢማዎቻቸውም ዘንድ ሙሉ ስምምነት የተረጋገጠ እንደሆነው ሁሉ ጂኒ በሰው ልጅ ላይ የሚገባ መሆኑም የአህሉ ሱና ወልጀማዓ አኢማዎች ዘንድ በሙሉ ስምምነት የተረጋገጠ ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{الذين يأكلون الربا لا يقومون إلا كما يقوم الذي يتخبطه الشيطان من المس}

{እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ብጤ እንጅ (ከመቃብራቸው) አይነሱም።}[2]ሶሒሕ በሆነ ሐዲሥም ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡- ("ሸይጧን በሰው ልጅ ውስጥ እንደ ደም ዝውውር ይሽከረከራል።")

ዐብደላህ ቢን ኢማም አሕመድ ቢን ሐንበል እንዲህ ብሏል፡- "ለአባቴ ሰዎች ጂኒ በተጠቂው አካል ውስጥ አይገባም ይላሉ አልኩት፤ እርሳቸውም 'ልጄ ሆይ! እየዋሹ ነው። በተጠቂው አንደበት የሚናገረው እኮ ሰይጣን ነው' አለኝ።" ይህ ኢማሙ የተናገሩት ነገር የታወቀ ነገር ነው። ምክንያቱም አንዳንዴ ሰይጣን የመታው ሰው በማይገባው ቋንቋ ሲናገር ይደመጣል፤ ሰውነቱም ግመል ቢመታበት ፋና በሚያሳድርበት አይነት ከፍተኛ ድብደባ ይመታል ይሁን እንጅ ተጠቂው ስለተናገረው ነገርም ይሁን ስለደረሰበት ድብደባ ምንም የሚሰማው ነገር አይኖርም። ተጠቂው ምንም ሳይታወቀው ጤነኛ ሰውንም ሊጎትት ይችላል።

ምንም ሳይታወቀው የተቀመጠበትን ምንጣፉን እየጎተተ፣ ቁሳቁሱን ሊያሽከረክር ከአንዱ

---

[1] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 275

[2] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ ቁጥር፡ 275

ቦታ ወደ ሌላ በታም ሊያዘዋውር፣ ሌሎችም ከዚህ ውጭ የሆኑ ነገሮችን ሲፈፅም በአይናቸው ላዩት ሰዎች በተጠቂው አንደበት እየተናገረ ያለው ተጠቂው እንዳልሆነ እና ነገራቶቹንም እያንቀሳቀሰ ያለውም ሰው እንዳልሆነ እርግጠኛ የሚያደርጉ እውነታዎችን ይመለከታል።

ከሙስሊም ኢማሞች መካከል ጂኒ ወደ ተጠቂ አካል የሚገባ መሆኑን የሚክድ ማንም የለም። ይህንንም ያስተባበለና ሸሪዓው ከዚህ ውጭ እንደሆነ የሞገተ በሸሪዓ ላይ ቀጥፏል። ከሸሪዓውም ይህንን የሚያስተባብል አንዳችም ነገር የለም። የሸይኹ ንግግር ተቋጨ።

ኢማም ኢብኑል ቀይም ረሒመሁላህ ዛዱል መዓድ ፊ ሀዲይ ኸይሪል ዒባድ በተባለው ኪታባቸው ቅጽ 4 ገጽ 66-69 ላይ እንዲህ ብለው ጠቅሰዋል፦ የሚጥል በሽታ ሁለት ዓይነት ነው፡ ከክፉ ምድራዊ መናፍስት የመጣ የሚጥል በሽታ እና ከመጥፎ መዛባት የመጣ የሚጥል በሽታ ሲሆን ይህ ሁለተኛው ዓይነት የህክምና ባለሙያዎች ስለ መንስኤውም ስለፈውሱም የሚያወሩበት ነው።

ከመጥፎ መናፍስት የመጣው የሚጥል በሽታን በተመለከተ (የፍልስፍናው) ሊቃውንቶች እና ጠቢቦቻቸውም አምነው የተቀበሉትና የማክዱት እውነታ ነው። ፈውሱን በተመለከተም ድርጊታቸውንና ሊፃረር በሚችልና ውድቅ በሚያደርግ ተቃራኒያቸው በሆነ ምጡቅ ደጋግ ልዑል መናፍስት ተፃራሪነት ክፋታቸውን በመመከት እንደሆነም ያምናሉ። ይህንንም በተመከከተ ሂፖክራተስ በአንዳንድ መጽሐፍቱ ላይ ስለሚጥል በሽታ ፈውስ እንዲህ በማለት ተናግሯል: "ይህ (እርሱ የጠቆመው መድሀኒት) የሚጠቅመው መንስኤው መዛባት ለሆነና ቁሳዊ መንስኤ ላለው የሚጥል በሽታ ብቻ ነው።

ከመናፍስት ለሚመጣ የሚጥል በሽታ ግን ይህ ህክምና የሚፈይድለት ነገር የለም። ይሁን እንጅ ወራዳነትና ንፍቅና ኩራት የሚመስላቸው መሀይማን እና ተራ ዝባዝንኬ ፈላስፎች ግን መንፈሳዊ መንስኤ ያለውን የሚጥል በሽታን ሊያወግዙ ይችላሉ። የሚጥል በሽታ የተጠቂውን አካል እንደሚጎዳ ላይቀበሉም ይችላሉ። ይህ ግን ከድንቁርና በቀር ሌላ ምንም መነሻ ምክንያት የለውም። አለበለዚያ በሕክምናውም ዓለም ይህ አይከሰትም ለማለት የሚያስችል ምንም ምክንያት የለማ። ያለው ተጨባጭም ያልነውን የሚያረጋግጥ ነው። ምናልባት ይህ መዛባቱ ሲበረታ የሚከሰት እንደሆነ ማመናቸው ሁል ግዜም ባይሆን አንዳንድ ጊዜ ትክክል የሚሆንበት አጋጣሚ አለ።" ንግግራቸውንም ሲቀጥሉ፦ "ወደ ኃላ አካባቢ የመጡት ወራዳነትና ንፍቅና የጠናባቸው ፈላስፎች በመዛባት የሚከሰተውን ካልሆነ በቀር የሚጥል በሽታ መኖሩን የማይቀበሉ ናቸው። ይሁን እንጅ ጤናማ አእምሮ ያለውና መናፍስትንና የሚያሳድሩትን ጫና በሚገባ የተረዳ ሰው የእነዚህ ሰዎች ድንቁርናና የአእምሮ ቁንፅልነት የሚያስቅ ሆኖ ያገኘዋል።

ታዲያ ይህንን ማከም የሚቻለው በሁለት መንገድ ነው፦ አንድም በታካሚው በኩል ሌላው

በመተካከሚያው በኩል ይሆናል። በተጠቂው በኩል ያለው ራስን አጠንክሮ እነዚህን መናፍስት ወዳስገኛቸውና ወደፈጠራቸው አካል በትክክል በመቅጣጨት እና ልቦናና አንደበት የተጠናከሩበት በሆነ ትክክለኛ የአላህን ጥበቃ በመሻት ነው። ይህ ትግል የፍልሚያ አይነት እንደመሆኑ መጠን ተፋላሚ ደግሞ ተፋላሚ ሊያሰኘው የሚችለው ሁለት ነገራቶችን ሲያሟላ ብቻ ነው፡- መሳሪያው በራሱ እጅግ ኃይለኛ መሆን እና ተፋላሚውም ብርቱ ሊሆን ይገባዋል። ከሁለቱ አንዱ ከተጓደለ መሳሪያ መያዙ ብቻውን ፋይዳ አይኖረውም። ጭራሽ ሁለቱም ከሌለስ?!

ልቦናው ከተውሒድ፣ ከተወኩል፣ ከተቅዋ እና ወደ አላህ ከሚደረግ ትክክለኛ መቅጣጨት ባዶ ይሆንና ሰላሙን የተነፈገ ይሆናል።

ሁለተኛው ከመድሀኒቱ በኩል ሲሆን እነዚህ ቀደም ብለን የጠቀስናቸው ሁለቱ ነገሮች አሁንም ሊሟሉ ይገባል። ከሚያክሙ አካሚዎች መካከል፡- (“ውጣ!”) በማለት ወይም፡ (ቢስሚላህ) በማለት ወይም ደግሞ፡- (“ላ ሐውላ ወላ ቁወተን ኢላ ቢላህ”) በማለት ብቻ የሚብቃቁ አካሚዎችም አሉ። ነቢዩም - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን - ሲያክሙ እንዲህ ነበር የሚሉት፡- (ውጣ አንተ የአላህ ጠላት! እኔ የአላህ መልዕክተኛው ነኝ!) እኔም በግሌ ሸይኻችን (ኢብኑ ተይሚያህ) የሚጥል በሽታ ወዳለበት ሰው እንዲህ የሚል መልዕክት አሲዘው ሰው ሲልኩበት አይቻለሁ፡ “ሸይኽ እንዳለሽ ይህ ላንቺ የተፈቀደ ቦታ አይደለምና ውጪ!" የሚል ትዕዛዝ ወደ ህመምተኛው በሰው ይልካል። በዚህም የታመመው ሰው ይነቃል፤ አንዳንዴ ህመምተኛው ራሱ ሊያነጋግራት ሁላ ይችላል።

አንዳንዴ ደግሞ መንፈሷ እልሀኛ ትሆንና በዱላ እንድትወጣ ይደረጋል፤ ህመምተኛው ሲነቃ ምንም ዓይነት ህመም የማይሰማው ሆኖ ይነቃል። ይህንንም እኛም ሆነ ሌሎች በተደጋጋሚ ያየነው ነገር ነው።" ብሎ ካለ በኋላ ንግግሩን ሲቀጥል "በጥቅሉ ይህ አይነቱ የሚጥል በሽታም ይሁን ፈውሱን የሚያወግዘው ከእውቀትም ከግንዛቤም ከማስተዋልም ድርሻው ጥቂት የሆነ ሰው ብቻ ነው።" አብዛኛውን ጊዜ ክፉ መናፍስት በሰው ላይ የሚሰፍሩት በሃይማኖታቸው በኩል ባላቸው ድክመት፤ ልቦናቸው ባዶ በመሆኑ እና ልሳናቸውም ከኢማን ነክ ከሆኑ ምሽጎችና ከነብያዊ ውዳሴዎች በመዘናጋቱ ምክንያት ነው። ታዲያ እነዚህም መናፍስቶች ሰውየውን ትጥቁን የፈታ ልፍስፍስ ምናልባትም ራቁቱን ሆኖ ሊያገኙት ሁላ ይችላሉ። የዚህ ግዜ ተፅዕኗቸውን ያሳድሩበታል። አላህ ይዘንላቸውና የሸይኹ ንግግር እዚሁ ተቋጨ።

ከጠቃቀስናቸው ሸሪዓዊ ማስረጃዎችና የአህለ ሱና ወልጀማዓህ ልሂቃን ሙሉ ስምምነት መነሻነት ጂኒ ወደ ሰው ልጅ የሚገባ መሆኑ በተመለከተ ያወገዙት ሰዎች ውድቅ አቋም እንዳላቸውና ሸይኽ ዐሊይ አጥጠንጧዊም በዚህ ረገድ ስህተት ላይ እንደወደቁ ለአንባቢው ግልፅ

ይሆንለታል።

ሸይኽ አጠንጧዊይ በንግግራቸው እውነታውን የሚጠቁማቸው ሲያገኙ ወደ ሐቁ እንደሚመለሱ ቃል ገብተዋልና ምናልባት የጠቀስነውን አንብበው ወደ እውነት እንደሚመለሱ ተስፋ እናደርጋለን። ሁላችንንም ወደ ቀናው ጎዳና ሊመራን ዘንድ አላህን እንማፀነዋለን። አን-ነድዋ ጋዜጣ በ14/10/1407 ዓመተ ሂጅራ ገፅ 8 ባተመው ዶ/ር ሙሐመድ ዒርፋን "እብደት" የምትለዋ ቃል ከህክምና መዝገበ ቃላት ተወግዳለች ማለታቸው እና ጂኒ ወደ ሰው ልጅ መግባቱ እና በሰውየው ልሳን የሚናገር የመሆኑ እውነታ ሳይንሳዊ ጽንሰ-ሀሳብ እንደሆነ የጠቀሰው መቶ በመቶ የተሳሳተ አባባል ነው። ይህ ሁሉ ሸሪዓዊ ጉድዮችን በተመለከተና የአህሉ ሱና ወልጀማዓህ ዑለሞች ያፀደቁትን እውነታ ካለመረዳት የመነጨ የእውቀት ማነስ ነው።

ይህ ጉዳይ በርካታ የህክምና ጠበብት ዘንድ የተደበቀ ጉዳይ ከሆነ ይህ ሊያመላክት የሚችለው ይህ ነገር እንደሌለ ሳይሆን ሃይማኖታቸውን በተመለከተ እውነታዎች፣ ባለአደራ እና የእውቀት ባለቤቶችም ለመሆናቸው የተመሰከረላቸው ሊቃውንት ያወቁትን ከዚያም ባሻገር የአህሉ ሱና ወልጀማዓዎች ሙሉ ስምምነት ያለበትን ጉዳይ የማያውቁ ከባድ ድንቁርና ያለባቸው መሆናቸውን የሚያመላክት ነው። ጉዳዩ ሙሉ ስምምነት (ኢጅማዕ) ያለበት ለመሆኑ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ ከመላው የእውቀት ባለቤቶች መገኘቱን እና በአቡ አል-ሐሰን አል-አሽዓሪይ ማጣቀሻነትም ከአህሉ ሱና ወልጀማዓዎች የተገኘ መሆኑን አስፍረዋል። በ 799 ሂጅራ የሞቱት አቡ ዐብደላህ መሐመድ ቢን ዐብዱላህ አሽ-ሺብሊ አል-ሐነፊይም እንዲሁ

በተከታዩ ኪታባቸው ከአቡል ሐሰን አል-አሽዓሪ አጣቅሰዋል፡ "አካሙል መርጃን ፊ ገራኢቢል አኽባር ወአሕካሙል ጃን" በተሰኘው ኪታባቸው፤ ሃምሳ አንደኛው ርእስ ስር ኢጅማዕ እንዳለበት ተቅሰዋል።

ቀደም ብለን በጠቀስነው የኢብኑል ቀይም ረሒመሁላህ ቃል፤ ጤናማ አእምሮ ያላቸውና አስተዋይ ሊቃውንቶቻቸው ይህንኑ እውነታ የሚቀበሉት እንጅ የማይቃወሙት እውነታ መሆኑን አሳልፈናል። የማይቀበሉት መሃይማኖቻቸውና ንፍቅና የተጠናወታቸው እንደሆኑም ቀደም ብለን ጠቅሰናል። በመሆኑም ውድ አንባቢ ሆይ! የነገርንህን እውነት ግምት ውስጥ በማስገባት እውነታውን ጠበቅ አድርገህ ያዝ በመሃይም ፈላስፎች ቃልም ይሁን በሌሎች በጉድዩ እውቀትም ማስረጃም ሳይኖራቸው ይልቁን ደናቁርት ፈላስፎችን በጭፍን በመከተል ያለመረጃ በሚናገሩ አትታለል። አሏሁል ሙስተዓን

## ማሳሰቢያ

ካሳለፍናቸው የረሱል የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ትክክለኛ ሐዲሦች እና የእውቀት ባለቤቶች ንግግር መረዳት እንደሚቻለው ጂኒውን በተጠቂው አንደበት ማናገር፣ መምከር፣ መገሠፅና ወደ እስልምና ዳዕዋ ማድረግ የጂኒውም ምላሽ መስጠት አላህ በሱረቱ ሷድ ስለ ሱለይማን ዓለይሂ ሰላም በሚከተለው መልኩ ከጠቀሰው ጋር የሚጣረስ አይደለም፡-

{رب اغفر لي وهب لي ملكا لا ينبغي لأحد من بعدي إنك أنت الوهاب،}

{«ጌታዬ ሆይ! ለእኔ ማር። ከእኔ በኋላ ለአንድም የማይገባንም ንግሥና ስጠኝ። አንተ ለጋሱ አንተ ብቻ ነህና»} ልክ እንደዚሁ ጂኒውን በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል ለመውጣትም እምቢተኛ ሲሆን መምታቱ ይህ ሁሉ ቀደም ብለን ከጠቀስነው የቁርኣን አንቀፅ ጋር የሚጋጭ አይደለም።

ይልቁንም ሰዎች ዘንድ በመካከላቸው እንዳለው በዳይን ከመግታትና ተበዳይን ደግሞ ከመርዳት አኳያ በመልካምም ከመተባበርና ከመጥፎም ከመከልከል አኳያ ግዴታ ነው። ቀደም ሲል በጠቀስነው ሶሒሕ ሐዲሥ ነብዩ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን - እንዲህ ማለታቸውን አሳልፈናል፡- (ለሀጩ እስኪዝረበረብ ድረስ አንቄ ያዝኩት።) በተከበረው እጃቸው - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን- ቀፍድደው ይዘውታል፤ እንዲህም ብለዋል፡- (ወንድሜ ሱለይማን ያደረገው ዱዓእ ባይኖር ኖሮ ሰዎች እንዲያዩት ታስሮ ነበር የሚያድረው።) ሙስሊም በዘገቡት ከአቡ ደርዳእ በተዘገበ ሐዲሥ ነብዩ - የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን - እንዲህ ብለዋል፡- (የአላህ ጠላቱ ኢብሊስ የእሳት ችቦ ይዞ ፊቴ ላይ ሊያደርግብኝ ሲመጣ ሶስት ጊዜ "አዑዙቢላሂ ሚንከ" (ትርጉሙም፡ ከአንተ በአላህ እጠበቃለሁ።) አልኩኝ። ከዚያም አከታትየ ሶስት ጊዜ "አልዓኑከ ቢልዕነቲላሂ ታማህ" (ትርጉሙም፡ በተሟላው የአላህ እርግማን እረግምሀለሁ) አልኩኝ። ከዚያም ልይዘው ፈለግኩኝ ፤ ወሏሂ ለወንድሜ ሱለይማን ዱዓእ ብየ እንጅ የመዲና ህፃናት የሚጫወቱበት እስረኛ አደርገው ነበር። በዚህ ረገድ የመጡት ሐዲሦች በርካታ ሲሆኑ ይህ የጠቃቀስነው የሊቃውንቱን ቃል ነው።

እስካሁን ያወሳነው ለሐቅ ፈላጊ የሚበቃውን ነገር እንዳሳለፍን ተስፋ አደርጋለሁ። እኛንም ሆነ ሌሎች ሙስሊሞችን ዲናችንን እንድንገነዘብና በእሱ ላይ እንዲያፀናን፤ ሁላችንንም በተግባርም በንግግርም ሐቁን በመግጠም ፀጋውን እንዲውልልን፤ እኛንም ሌላውንም ሙስሊም ያለ እውቀት ከመናገርም ይሁን እውቀታችን ያልደረሰበትን ነገር የምናወግዝ ከመሆንም እንዲጠብቀን አላህን በመልካም ስሞቹ እና በምሉእ ባህሪያቱ እማፀነዋለሁ።

የአላህ ሰላትና ሰላም አገልጋይ ባርያው እና መልዕክተኛው በሆኑት ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸው፣

በባልደረቦቻቸውና በቅን ተከታዮቻቸው ሁሉ ይስፈን።

# ይዘት | المحتويات

መቅድም ...... 3
የድግምት እና ጥንቆላ ብይን እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮች ...... 5
ሚስት ባሏ ላይ ያሰራችው ድግምት ...... 14
ሟርተኞችንና አጭበርባሪዎችን መጠየቅ ያለው ኢስላማዊ ፍርድ ...... 16
ጂን በሚጠቀም የህዝብ ሐኪም የሚደረግ ሕክምና ...... 18
የድግምት ሸሪዓዊ ፈውስ ...... 19
ጂኒ በሰው አካል ውስጥ የሚገባ ስለመሆኑ እውነታውን ግልጽ ማድረግ እና ያንን ላስተባበሉ ሰዎች ምላሹን መስጠት ...... 23
ማሳሰቢያ ...... 34




ምስጋና ለአሏህ ይገባው፤ ተጠናቀቀ